# የመምህሩ መምሪያ

## የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ደረጃ 1 እና 2

## ተከታታይ ትምህርቶች 7 - 12

www.besweb.com

## የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች አገልግሎት

በሕግ የተመዘገበ የዩናይትድ ኪንግደም ለጋሽ ድርጅት (የምዝገባ ቁጥር 1096157)

**ተልእኮ**

በአለም ዙሪያ ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ እንዲሁም በዚህ ዘመን ያለውንና የወደፊቱን ትውልድ የእግዚብሔርን ቃል ለማስተማር የሚረዱ ተከታታይ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን በማዘጋጀት ሰዎችን ማገልገልና ለአገልግሎት ብቁ ማድረግ።

**ራዕይ**

የተለያዩ የኮሙኒኬሽን አይነቶችን ስራ ላይ በማዋልና ዋና ዋና እሴቶቻችን ከሚጋሩ ግለሰቦች ጋር አብሮ በመስራት በተለየዩ የዓለም ቋንቋዎች የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች ዝግጅትን ማበረታታት።

## አጠቃላይ መረጃ

**የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች አገልግሎት ተግባራት ምንድናቸው?**

የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች አገልግሎት "ዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ"፣ "አዲስ ሕይወት" እና "ቃራሚዎች" በሚል ርዕስ የሚታወቁ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን በእንግሊዝኛ ያሳትማል። እንዲሁም በምድረ እንግሊዝና በሌሎች የዓለም ክፍሎች በፖስታ ቤቶች አማካኝነት በመላላክ እነኝህን ትምህርቶች የሚሰጡ የርቀት ትምህርት ቤቶችንና ሌሎች ድርጅቶችን በጉብኝት፣ በምክር፣ በኔትወርኪንግና በስልጠና ያግዛል። የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች አገልግሎት በአሁኑ ጊዜ በትርጉም፣ በዲዛይን፣ በሕትመትና ትምህርቶችን በማሰራጨት ከሚሰሩና በሌሎች አገሮች ውስጥ ከሚገኙ ቡድኖች ጋር አብሮ ይሰራል። ለሁሉም ተማሪዎች ትምህርቶቹ በነፃ እንዲዳረሱ ማድረግም ሌላው የመጽሐፍ ትምህርቶች አገልግሎት ተግባር ነው።

የመጽሐፍ ቅዱስ ጊዜ ትምህርቶች በመጀመሪያ ጥቅም ላይ የዋሉት በደቡብ አየርላንድ ከ50 ዓመታት በፊት ነበር። የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች አገልግሎት በእንግሊዝኛና በሌሎች የውጭ አገር ቋንቋዎች የሚዘጋጁ የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን የኤዲቶሪያል ኃላፊነት ይወስዳል። የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች ሕትመት በኤ 4 ፎርማት ሆኖ በአንዳንድ አካባቢዎች የሚገኙ ተማሪዎች በአራት ሳምንት አንድ ጊዜ ትምህርቶችን ለመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ማዕከል ለእርማት መላክ እንዲችሉ ያግዛቸዋል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ለቤት ለቤት ጆማ ወንጌል (የተሐድሶ ንቅናቄ) ምስጋና ይግባውና በቤልፋስት የ6 ወራት ትምህርቶች በኤ 5 ፎርማት ማዘጋጀት ተችሏል። ይህም ትምህርቶች በት/ቤቶችና በየአብያተ ክርስቲያናቱ በቀላሉ ጥቅም ላይ እንዲውሉ አስችሏል። ይህ ደግሞ ጥሩ የፖስታ አገልግሎት በሌለባቸው አካባቢዎች ውጤታማ ሆኗል።

የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች አገልግሎት ኮርሶችን ልዩ የሚያደርጋቸው የቤት ለቤት ወይንም ደግሞ በቤተ ክርስቲያንና በት/ቤቶች የሚካሄዱ የቡድን ጥናቶችን ግንዛቤ ውስጥ አስገብተውና በሚገባ የታቀደ ሲለበስን ተከትለው ተማሪዎች ጥናታቸውን እድሜያቸው 20 ዓመት እስኪሆነው ድረስ እንዲቀጥሉ ስለ ሚረዷቸው ነው። ለየእድሜ ደረጃው የሚመጥኑ በአምስት ደረጃዎች የተከፋፈሉ ትምህርቶች ቀርበዋል። ቅድመ መደበኛ ትምህርት፣ ከ5-7 ዓመት፣ ከ8-10 ዓመት፣ ከ11-13 ዓመት፣ ከ14-16 ዓመት። ለእያንዳንዱ የእድሜ ክልል የሶስት ዓመት ሲለበስ ተዘጋጅቷል። (ገፅ አራትን ይመልከቱ።) እያንዳንዱ የእድሜ ክልል ባሉት ችሎታዎች መሠረት ይለያያል። የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች ልጆች የእግዚአብሔርን ቃል እንዲያጠኑ እድል ይፈጥርላቸዋል። ይህም የተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮችን እንዲማሩና ወንጌልን በሕይወታቸው ለመተግበር በሚያደርጉት ጥረት የሚገጥሟቸውን ተግዳሮቶች መጋፈጥ እንዲችሉ በማገዝ ነው።

የእነኝህ ትምህርቶች ኮፒዎች በእንግሊዝኛ ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች አገልግሎት ዌብ ሳይት **(www.besweb.com)** ላይ ማውረድ ይቻላል። የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች አገልግሎት አብረውት በአጋርነት መስራት ለሚፈልጉ ሰዎች የሚጠቅሙ ዶክሜንቶች አሉት። እነኝህ ዶክሜንቶች በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች አገልግሎት ዌብ ሳይት ላይ ይገኛሉ።

## የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች አገልግሎት አድራሻዎች

**ዓለም አቀፍና የሰሜን አየርላንድ ፀሐፊ (የሁሉም ትምህርቶች አከፋፋይ)**
Mr S Balmer, 37a Belmore Street, Enniskillen, Northern Ireland BT74 6AA
ስልክ: 0286 632 2462
ኢሜይል: sam@besweb.com

**የዩናይትድ ኪንግደም ፀሐፊ**
Mr Stephen Gillham, 32 Firs Glen Road, West Moors, Ferndown, Dorset BH22 0ED
ስልክ: 01202 873500
ኢሜይል: stephen@sgilllham.co.uk

**ዌብ ሳይት**: www.besweb.com
**የኢሜይል አድራሻ**: info@besweb.com

## *ለመምህራን መምሪያዎች*

*የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች በመጀመሪያ ሲዘጋጁ በፖስታ በመላላክ ለማስተማር ታስበው ነበር። ለዚህም ይረዳ ዘንድ የፖስታ መጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት ማዕከላት ተቋቁመው ነበር። ነገር ግን የፖስታ አገልግሎት አስተማማኝ ባልሆነባቸው እስከጭራሹንም እየቀረ በሚሄድባቸው ስፍራዎች በተለይም ደግሞ በአፍሪካና በሕንድ እንዲሁም በሌሎች የዓለማችን ክፍሎች በስፋት ጥቅም ላይ እየዋሉ ነው። በዚህ ሁኔታ ውስጥ የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን ለሚጠቀሙ የማስተማሪያ መምሪያዎችም ተዘጋጅተዋል። በዚህ ጥራዝ ውስጥ የተዘጋጁት የመምህሩ መምሪያዎች ታሳቢ ያደረጉት ደረጃ 1 እና 2ን በግምት እድሜያቸው ከ5-10 ዓመት የሆኑ ልጆችን ነው።*

*እያንዳንዱ የመምህሩ መምሪያ ልክ **በዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ** ትምህርት ውስጥ የተጠቀሱ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን ተከትሎ የተዘጋጀ ነው። የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችና መምሪያዎቻቸው በየሳምንቱ እንዲጠኑ ተደርገው ተዘጋጅተዋል። የሚያዚያ ትምህርቶች በተለይ ከፋሲካ ጋር የተገናኙ ትምህርቶች ሲሆኑ የታህሳስ ትምህርቶች ደግሞ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ጋር የተገናኙ ናቸው።*

*በአንዳንድ ቦታዎች በኤ 4 የወረቀት መጠን የሚዘጋጀውን ሳምንታዊ ሕትመት ሲጠቀሙ በሌሎች ቦታዎች ደግሞ 24 ትምህርቶችን የያዘውንና በኤ 5 የወረቀት መጠን የተዘጋጀውን ጥራዝ ይጠቀማሉ። መምህሩ ወይንም ደግሞ የጥናቱ/የትምህርቱ መሪ በኤ 4 የወረቀት መጠን ትምህርት ያድላል። ትምህርቱም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ወይንም ደግሞ በት/ቤት ይሞላል ወይንም ደግሞ ወደ ቤት ይወሰዳል። ከዚያም በተከታዩ ሳምንት ይመለሳል። በወሩ መጨረሻ መምህሩ ወይንም የጥናቱ/የትምህርቱ መሪ ትምህርቶችን ይሰበስብና ያርማቸዋል። ነጥብም ይሰጣቸዋል። በተቻለ መጠንም ከእርማት በኋላ ለተማሪዎች መመለስ አለበት።*

*የተዘጋጁት ጥራዞች ጥቅም ላይ ከዋሉ በየሳምንቱ መጨረሻ እየተሰበሰቡ ይታረማሉ። በብዙ ምክንያቶች ይህ አስቸጋሪ እንደሆነ እንረዳለን። ስለዚህም በክፍል ውስጥ ጥራዞቹ ለተማሪዎች ይከፋፈላሉ። በዚህ ጊዜ መምህሩ/መሪው ከተማሪዎች ጋር አብሮ ይሰራል። ተማሪዎችም የጓደኞቻቸውን ስራዎች ያርማሉ፣ ነጥብም ይሰጣሉ። ከጥራዞቹ በስተጀርባ ለእያንዳንዱ ነጥብ መመዝገቢያ ሰንጠረዥ እንዲሁም ተማሪው ስላሳየው እድገት አስተያየት መስጫ ቦታ አለ። እንዲሁም ከጥራዙ በስተመጨረሻ ሰርተፊኬት ተያይዟል። ይህ ሰርተፊኬት በቀላሉ ከጥራዙ ላይ ሊገነጠል የሚችል ሲሆን ተማሪው ባለፉት 6 ወራት ከመቶ ያገኛቸውን ውጤቶች ይይዛል።*

## *ለመምህራን የተደረገ ዝግጅት*

*መምህራን በራሳቸው ዘዴ ወይንም መንገድ፣ ተነሳሽነትና ሀሳብ ላይ የተመሠረተ አንዳችም ነገር እንዲያደርጉ አንጠብቅም። ለእንደዚህ አይነት ጉዳይ ምንም ቦታ አንሰጥም። የሚከተሉት ሀሳቦች የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን ለመጠቀም የሚያስፈልጉ ጠቃሚ ሀሳቦች ናቸው።*

- **ከታሪኩ ጋር በሚገባ ራስን ማስተዋወቅ** - ከመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮችና በተጓዳኝ አብረውት ከሚሄዱት የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች ጋር በተቻለ መጠን ራሳቸውን ማስተዋወቅ አለባቸው። መምህሩ የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን ከማስተማሩ በፊት ራሱ አጥንቶ ቢያጠናቅቅ ተመራጭ ነው። ለእያንዳንዱ ትምህርት የተዘጋጁት መምሪያዎችም በእቅድ ወቅት ስለ ሚረዱ በጥንቃቄ ሊታዩ ይገባል።
- **ትምህርቶችን በሚገባ መረዳት** - ከእያንዳንዱ የትምህርት እቅድ በላይ *"በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።"* የሚሉ ቃላት ይገኛሉ። እነኝህም መምህሩ ገለፃውን ካጠናቀቀ በኋላና ተማሪዎችም ያንን የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ከተማሩ በኋላ የሚጨብጧቸውን ሁለት አላማዎች የያዙ ናቸው። የመጀመሪያው አላማ ከታሪኩ ስለ ቀሰሙት እውቀት ነው። ሁለተኛው ደግሞ ተማሪዎች ስላገኙት እውቀት እንዲያሰላስሉና በተቻለ መጠንም ምላሽ እንዲሰጡና ከሕይወታቸው ጋር እንዲያዛምዱት ያበረታታል። እነኝህ የመማር አላማዎች በተሰጠው ትምህርት ውስጥ ያለውን ዋና ፅነሰ ሀሳብ/እውነት የያዙ ናቸው። መምህራንም ራሳቸውን እንዲሁም የመማር የማስተማር ሂደቱን ለመገምገም ሊጠቀሙባቸው ይችላሉ።
- **አስተዋውቁት/መግቢያ** - *ሁሉንም ትምህርቶች የምንጀምረው ከራሳቸው ከተማሪዎች ልምምድና ካሉበት ሁኔታ በመነሳት ነው። ታሪኮችን በመግቢያው ውስጥ ለማስተዋወቅ የተለያዩ ዘዴዎችን አቅርበናል። በዚህም ልጆች በትምህርቱ ማስጀመሪያ ነጥብ ላይ በመስተጋብር የተሞላ ውይይት እንዲያካሂዱ እናስችላቸዋለን።*
- **የማስተማር ጊዜ** - *የታሪኩን ቁልፍ ነጥቦች አቅርበናል። መምህራን ታሪኮቹን በሚያስተምሩበት ወቅት እነኝህን ቁልፍ ነጥቦች እንደማያነሷቸው ተስፋ እናደርጋለን። ሆኖም በሚያስምሩበት ወቅት ራሳቸውን ከታሪኩ ጋር በሚገባ አስተዋውቀው ውጤታማ በሆነ መንገድ ለማስተማር ይጠቀሙባቸዋል። መምህሩ በትምህርቱ ውስጥ ያለውን ታሪክ ተማሪዎቹ በሚገባ እንዲረዱ ማድረግ አለበት። እንዲሁም ልጆቹ ታሪኩን ከተገነዘቡት በኋላ መስጠት ስላለባቸው ምላሽ አቅጣጫ ይጠቁማቸዋል። ከእያንዳንዱ ትረካ ጋር አብሮ የሚሄዱ ማብራሪያዎችንም አብረን ማቅረቡ ተገቢ ስለሆነ ይህንኑ አድርገናል። እነኝህም በኢታሊክስ (ITALICS) ተፅፈው ቀርበዋል።*
- **የመማር ጊዜ** - ከእያንዳንዱ ታሪክ ጋር አብሮ የተያያዘ ቁልፍ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ አለ። አንዳንድ ጊዜም ሁለት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ተያይዘዋል። ምክንያቱም ተጨማሪው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ተማሪዎች በቀላሉ መማር እንዲችሉ ያግዛቸዋል። ልጆች እነኝህን ቁልፍ ጥቅሶች እንዲማሩ እንዲሁም በተደጋጋሚ እንዲያስታውሱት እንደሚደረግ ተስፋ እናደርጋለን። ይህም ልጆች የቁልፍ መጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች እውቀት ግንባታ ማድረግ እንዲጀምሩ ይረዳቸዋል።
- **ማጠናቀቅ** - *በት/ቤት ውስጥ ተማሪዎች ሰርቶ ማሳያ/የመለማመጃ ጥያቄዎችን ለማጠናቀቅ የሚያስፈልጋቸውን የችሎታ ልክና መምህሩ በዚህ ረገድ ለተማሪዎቹ ሊያደርግላቸው የሚችለውን የእገዛ መጠን በተመለከተ ግንዛቤ ሊኖራችሁ ይገባል። አንዳንዶች መምህሩ ታሪኩን ካነበበላቸውና ከታሪኩ ጋር በሚገባ ከተዋወቁ በኋላ ወደ ስራ ይገባሉ። ሌሎች ልጆች ደግሞ ታሪኩን ራሳቸው ማንበብ ይችላሉ። በሁለቱም መንገዶች ዋናው ሀሳብ ጥያቄዎቹን ለመስራት በተሰጠው ትዕዛዝ ላይ የልጆቹ አትኩሮት እንዲያርፍ ማድረግ ነው። የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን ከት/ቤት ውጪ በሌሎች ቦታዎች የምትጠቀሙ ከሆነ ተማሪዎቻችሁን ባሉበት ቦታ በአካል ተገኝታችሁ መርዳት መቻል አለባችሁ። አለበለዚያ ተማሪዎቻችሁ ትምህርቱን እንደፈተና ወይንም ደግሞ*

የግድ መጠናቀቅ እንደላበት ስራ አድርገው ሊቆጥሩት ይችላሉ። አስደሳች መሆን አለበት። ለዚህም ተማሪዎች እየሰሩ ባለበት ወቅት ማበረታታት አስፈላጊ ነው።

- **የክለሳ ጊዜ** - በተቻለ መጠን ተማሪዎች በምን ያህል መጠን ትምህርቱን አውቀውታል የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ የሚረዱንን አጫጭር ሙከራዎችን መስጠት ወይንም አስፈላጊ መሆኑን እንመክራለን። ይህም ትምህርቱን ለመከለስና የተማሪዎችን የመማር ፍጥነት ለማገዝ ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው።
- **ማሳየት** - በአንዳንድ ሁኔታዎች የቪዡዋል (የእይታ) ትምህርት መርጃዎች በቀላሉ ላይገኙ ቢችሉም በተቻለ መጠን ለሚታዩ ስዕሎች ወይንም ደግሞ  ለሌሎች ቁሳቁሶች ትኩረት መስጠትና በተግባር ማዋል ተማሪዎች ትምህርቱን በቀላሉ መረዳት እንዲችሉ ይረዳቸዋል። በትረካ ወቅት የእይታ ትምህርት መርጃዎች ትልቅ እገዛ ያደርጋሉ። አስፈላጊ የሆኑ ስዕሎችን በተመለከተ መረጃ ከተፈለገ ከሚከተለው ዌብ ሳይት ማግኘትና ስዕሎችንም ማውረድ ይቻላል። [www.freebibleimages.org (FBI)] ሌላው የእይታ መርጃዎችን የምናገኝበት ምንጭም Eikon Bible Art [info@eikonbibleart.com] ዌብ ሳይት ነው። ሆኖም ከዚህ ዌብ ሳይት የምናገኛቸው ምንጮች በሽያጭ የሚገኙ ናቸው። የፎቶ ኮፒ ማሽን ባለበት አንዳንድ ስእሎች ሊተልቁ ቀለም ሊቀቡና በትምህርት ወቅት ጥቅም ላይ ማዋል ሊውሉ ይችላሉ።

**ቁልፍ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን የማስተማር ጊዜ**

1) ጥቅሱ በወረቀት ወይንም በጥቁር ሰሌዳ ላይ ሊፃፍ ይችላል። ይህም የተለያዩ ቃላትን በማጉደል የሚደረግ ነው። ይህም ሁሉም የጥቅሱ ቃላት በሙሉ እስኪጠፉና ተማሪዎችም ጥቅሱን በቃላቸው መድገም እስኪችሉ ድረስ ነው።
2) ቁልፍ ጥቅሱን ለማስተዋወቅ የሚከተሉትን ማድረግ ትችላላችሁ።
   ሀ) በሁለት ቡድኖች መስራት (በገመድ የመስቀል ዘዴ)  – የቁልፍ ጥቅሱ የተለያዩ ፊደላት ተቀንሰው በምትካቸው ክፍት ቦታዎች አሉ። ልጆችም የትኞቹን ቃላት ቢጠቀሙ ጥቅሱን ማሟላት እስከሚችሉ ድረስ ይሰራሉ። ይህም ከመካከላቸው አንደኛው ልጅ ጥቅሱን እስከሚለየው ድረስ ይቀጥላል።
   ለ) ጥቅሱን ቀድሞ መፈለግ። መጽሐፍ ቅዱስ በቀላሉ የሚገኝ ከሆነ ተማሪዎች ቁልፍ ጥቅሱን ይፈልጋሉ። መጀመሪያ ጥቅሱን ያገኘው ልጅ አሸናፊ ይሆናል።

**ጊዜን ማቀድ**

- **ቅደም ተከተል** ለሁሉም የማስተማሪያ መምሪያዎች ተመሳሳይ ቅደም ተከተል እንጠቀማለን። ሆኖም ይህን ቅደም ተከተል መምህራን እንደአስፈላጊነቱ ሊቀያይሩት ይችላሉ።
   1. መግቢያና ትረካ - በግምት  15 ደቂቃ
   2. ቁልፍ ጥቅሱን የማስተማር ጊዜ – ከ5 እስከ10 ደቂቃ
   3. ስርቶ ማሳያውን ማጠናቀቅ - 20 ደቂቃ
   4. መልመጃና ሌሎች ስራዎች  5-10 ደቂቃ

ይህን አባባል ሁሌም አስታውሱት።

“የነገራችሁኝን እረሳለሁ።
የምታሳዩኝን አስታውሳለሁ።
አብሬያችሁ ስሰራ በሚገባ እረዳለሁ።”

## የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች ሲለበስ

| | ደረጃ 0 (ቅድመ መደበኛ ትምህርት)<br>ደረጃ 1 (ከ5-7 ዓመት)<br>ደረጃ 2 (ከ8-10 ዓመት) | ደረጃ 3 (ከ11-13 ዓመት) | ደረጃ 4 (14 ዓመትና ከዚያ በላይ) |
|---|---|---|---|
| የጀማሪዎች ተከታታይ ትምህርቶች | 1. የጀማሪዎች ትምህርት - መግቢያ<br>2. ሀ1 - የሉቃስ ወንጌል<br>3. ሀ2 - የሉቃስ ወንጌል<br>4. ሀ2 - የሉቃስ ወንጌል | 1. የጀማሪዎች ትምህርት - መግቢያ<br>2. ሀ1 - የሉቃስ ወንጌል<br>3. ሀ2 - የሉቃስ ወንጌል<br>4. ሀ2 - የሉቃስ ወንጌል | 1. የጀማሪዎች ትምህርት - መግቢያ<br>2. ሀ1 - የሉቃስ ወንጌል<br>3. ሀ2 - የሉቃስ ወንጌል<br>4. ሀ2 - የሉቃስ ወንጌል |
| ሀ/ ተከታታይ ትምህርቶች | 1. ፍጥረት<br>2. ኖህ<br>3. ጴጥሮስ<br>4. ጴጥሮስ - መስቀሉ<br>5. አብርሃም<br>6. አብርሃም<br>7. ጴጥሮስ<br>8. ጴጥሮስ<br>9. ያዕቆብ<br>10. የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች<br>11. ጳውሎስ<br>12. የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ታሪክ | 1. ፍጥረት<br>2. ኖህ<br>3. ጴጥሮስ<br>4. ጴጥሮስ - መስቀሉ<br>5. ጴጥሮስ<br>6. አብርሃም<br>7. ያዕቆብ<br>8. ፀሎት<br>9. ጳውሎስ<br>10. ጳውሎስ<br>11. ጳውሎስ<br>12. የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ታሪክ | 1. ፍጥረትና ውድቀት<br>2. ዘፍጥረት የመጀመሪያዎቹ ክንዋኔዎች<br>3. ጴጥሮስ<br>4. ጴጥሮስ - መስቀሉ<br>5. ጴጥሮስ<br>6. አብርሃም<br>7. ያዕቆብ<br>8. የክርስቲያን ሕይወት<br>9. ጳውሎስ<br>10. ጳውሎስ<br>11. ጳውሎስ<br>12. የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ታሪክ |
| ለ/ ተከታታይ ትምህርቶች | 1. የክርስቶስ የቀደመው ሕይወቱ<br>2. ተአምራት<br>3. ቢታኒያ<br>4. መስቀሉ<br>5. ምሳሌዎች<br>6. ዮሴፍ<br>7. ዮሴፍ<br>8. ኢየሱስ የተገናኛቸው ሰዎች<br>9. ሙሴ<br>10. ሙሴ<br>11. ሙሴ<br>12. የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ታሪክ | 1. ምሳሌዎች<br>2. ተአምራት<br>3. ቢታኒያ<br>4. መስቀሉ<br>5. የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች<br>6. ዮሴፍ<br>7. ዮሴፍ<br>8. የወንጌል ፀሐፊዎች<br>9. ሙሴ<br>10. ሙሴ<br>11. ሙሴ<br>12. የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ታሪክ | 1. ምሳሌዎች<br>2. ተአምራት<br>3. ቢታኒያ<br>4. መስቀሉ<br>5. የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች<br>6. ያዕቆብና ቤተሰቡ<br>7. ዮሴፍ<br>8. የሐዋርያት ስራ 2፡42 ከፊት ለፊት ያለው መንገድ<br>9. ሙሴ<br>10. ሙሴ<br>11. ሕግ<br>12. የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ታሪክ |
| ሐ/ ተከታታይ ትምህርቶች | 1. ዳንኤል<br>2. ተጨማሪ ተአምራት<br>3. ኢየሱስ የተገናኛቸው ሰዎች<br>4. የክርስቶስ ሞት<br>5. ሩትና ሳሙኤል<br>6. ዳዊት<br>7. ዳዊት<br>8. ኢያሱ<br>9. ኤልያስ<br>10. ኤልሳዕ<br>11. ዮናስ<br>12. የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ታሪክ | 1. ዳንኤል<br>2. ኢየሱስ የተገናኛቸው ሰዎች<br>3. ተጨማሪ ተአምራት<br>4. የክርስቶስ ሞት<br>5. ሩት<br>6. ሳሙኤል<br>7. ዳዊት<br>8. ኢያሱ<br>9. ኤልያስ<br>10. ኤልሳዕ<br>11. እግዚአብሔር የተጠቀማባቸው የብሉይ ኪዳን ዘመን ሰዎች<br>12. የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ታሪክ | 1. ዳንኤል<br>2. የኢየሱስ አባባሎች<br>3. የጌታ ኃይል<br>4. የክርስቶስ ሞት<br>5. ሩት<br>6. ሳሙኤል<br>7. ዳዊት<br>8. ኢያሱ<br>9. ኤልያስ<br>10. ኤልሳዕ<br>11. ተጨማሪ የብሉይ ኪዳን ባሕርያት<br>12. የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ልደት ታሪክ |

## <u>ሀ7 ታሪክ 1</u>

**የጴጥሮስ ስብከት – ይህ ታሪክ ጴጥሮስ በመንፈስ ቅዱስ ተረድቶ እንዴት ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሰበከ የሚናገር ታሪክ ነው።**

| | |
|---|---|
| | **በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>• ደቀ መዛሙርቱ መንፈስ ቅዱስ እንደሚያስፈልጋቸው እንማራለን።<br>• ኢየሱስ ክርስቶስን እንደአዳኝ በተቀበለ በእያንዳንዱ አማኝ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ እንዳለ እንማራለን።<br>**ቁልፍ ጥቅስ** **የሐዋርያት ሥራ 2: 36**<br>**የጥናት ክፍል :** **የሐዋርያት ሥራ 2: 1–14, 36-39** |
| *መግቢያ* | • *መንፈስ ቅዱስን ለማስተዋወቅ ጥያቄዎችን ተጠቀሙ። ነፋስን ማየት ትችላላችሁ? በፍፁም! ታዲያ ንፋስ መኖሩን በምን ታውቃላችሁ? በሚያደርጋቸው ነገሮች ነፋስ እንዳለ እናውቃለን። ከክፍል ውጪ ማየት የምትችሉ ከሆነ ንፋስ እንዳለ የሚጠቁሙ መረጃዎችን ፈልጉ።*<br>• ልጆች የፋሲካ ታሪክን እንዲያስታውሱ አድርጓቸው። ኢየሱስ ሞቷል ደግሞም ከሞት ተንስቷል። ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ሰማይ ከማረጉ በፊት ለደቀ መዛሙርቱ በአይን የማይታይ ልዩ ረዳት እንደሚልክላቸው ቃል ገባላቸው።<br>• *ይህ ረዳት መንፈስ ቅዱስ ነው። መንፈስ ቅዱስ በእያንዳንዳቸው ደቀ መዛሙርቱ ውስጥ ይኖራል። ልክ እንደንፋሱ በአይናቸው አያዩትም። በውስጣቸው መኖሩን የሚያውቁት በሕይወታቸው በሚያስከትላቸው ለውጦች ነው።* |
| *የማስተማር ጊዜ* | • አንድ ቀን ልክ ኢየሱስ ወደ ሰማይ እንዳረገ ለደቀ መዛሙርቱ በኢየሩሳሌም በአንድ ቤት በአንድነት ተሰብስበው ነበር። (**የሐዋርያት ሥራ 2: 1-4**) በድንገትም ቤቱ እንዳለ በድንገት በትልቅ የነፋስና ነውጥ ድምፅ ተሞላ። በዚያ ቤት ውስጥ በነበረ በእያንዳንዱ ሰው ራስ ላይም የእሳት አምድ የሚመስል ነገር ተቀመጠበት። መንፈስ ቅዱስ መጣ! *ለደቀ መዛሙርቱ ምን ተሰማቸው ትላላችሁ? (ኢየሱስ የሰጣቸው የተስፋ ቃል እውን ስለሆነ ደስታ፣ መገረም ወዘተ... ይሞላሉ።)*<br>• በተለያዩ ቋንቋዎች ሲናገሩ ራሳቸውን አገኙ! *በመሠረቱ መናገር የምንችለው ከወላጆቻችን በልጅነታችን የወረስናቸውን ወይንም የተማርናቸውን ቋንቋዎች ነው። የኢየሱስ ደቀ መዛመርት ዛሬ የሚናገሯቸውን ቋንቋዎች አልተማሯቸውም።* እነኝህ ምልክቶች በሙሉ መንፈስ ቅዱስ መውረዱን የሚያሳዩ ምልክቶች ናቸው። *በዚህ ደቀ መዛሙርቱ ባለቡት ቤት አጠገብ ብታልፉ ምን ይሰማችኋል?*<br>• በዚያ የሚያልፉ ሰዎች በሰሙት ድምፅ ግራ መጋባትና መደነቅ ሞላባቸው! (**የሐዋርያት ሥራ 2: 5–13**)<br>• ጴጥሮስ ይህ ምን እየሆነ እንዳለና እንዲሁም ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ለመናገር ጥሩ አጋጣሚ እንደሆነ ተረዳ። (**የሐዋርያት ሥራ 2: 36–39**) *ለበርካታ ሕዝብ መስበክ አዳጋች የሚሆንባቸውን ምክንያቶች ተወያዩባቸው። (አስፈሪ፣ የምንናገባቸውን አረፍተ ነገሮች በእርግጠኝነት አለማወቅ፣ ተሰባኪዎች ምን ሊሉ ወይንም ሊያደርጉ እንደሚችሉ እርግጠኛ አለመሆን ወዘተ...)* ጴጥሮስ በመንፈስ ቅዱስ ስለ ተረዳ ይህን ማድረግ ችሏል።<br>• *የጴጥሮስ ስብከት አድማጮች ከኃጢአታቸው መዳን ያስፈልጋቸው ነበር። እኛም እንዲሁ!*<br>• *ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ለሚያምንበት ሁሉ መንፈስ ቅዱስ እንደሚሰጥ አስረዷቸው። መንፈስ ቅዱስ ለሌሎች ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ እንድንናገር ይረዳናል።*<br><br>**የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን አጠናቁ።** |
| *የመማር ጊዜ* | ቁልፍ ጥቅሱን እንደአስፍላጊነቱ አስተምሩ፣ አብራሩ። - **የሐዋርያት ሥራ 2: 36**. ይህ ጴጥሮስ በስብከቱ ከተናገረው የተወሰደ ነው። አድማጮቹ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደገደሉትና እግዚአብሔር ግን ከሞት እንዳስነሳውና አሁን ሕያው እንደሆነ ነገራቸው። ይህም ኢየሱስ ክርስቶስ ጌታና ክርስቶስ እንደሆነ ማስረጃ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ ተራ ሰው አይደለም። |
| *የክለሳ ጊዜ* | • *መንፈስ ቅዱስ ሲወርድ ደቀ መዛሙርቱ የት ነበሩ?*<br>• *መንፈስ ቅዱስ ሲወርድ የተሰማው ድምፅ ምን ይመስል ነበር?*<br>• *ደቀ መዛሙርቱ ያዩት ምን ነበር?*<br>• *ልክ በመንፈስ ቅዱስ እንደተሞሉ ለደቀ መዛሙርቱ ማድረግ የቻሉት ነገር ምን ነበር?*<br>• *እየሆነ ያለውን ነገር የሰሙት እነማን ነበሩ?*<br>• *እየሆነ ያለውን ነገር ቆሞ ያስረዳው የትኛው ደቀ መዛሙር ነበር?*<br>• *ጴጥሮስ የተናገረው ስለ ማን ነበር?*<br>• *ስለ ኃጢአታቸው ለስብከቱ አድማጮች ምን እንዲያደርጉ ነገራቸው?*<br>• *ይህን ቢያደርጉ የሚቀበሉት ስጦታ ምን ነበር?*<br>• *ዛሬ መንፈስ ቅዱስ በውስጣቸው የሚኖር ሰዎች ምን አይነት ሰዎች ናቸው?* |

## *ሀ7 ታሪክ 2*

## ጴጥሮስ ሽባውን ሰው ፈወሰው። – ይህ ታሪክ ስለ እግዚአብሔር የፈውስ ኃይል ይናገራል።

**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**

- የኢየሱስ ኃይል ጴጥሮስንና ዮሐንስን ተጠቅሞ ሽባውን ሰው ተረተረው።
- ጴጥሮስና ዮሐንስ ሽባውን ሰው መርዳት ፈለጉ። እኛም እንዲሁ ሌሎችን የመርዳት ፍላጎት ሊኖረን ይገባል።

**ቁልፍ ጥቅስ** **ደረጃ 1 - የሐዋርያት *ሥራ* 3: 6, ደረጃ 2 - የሐዋርያት *ሥራ* 3: 16**
**የጥናት ክፍል :** **የሐዋርያት *ሥራ* 3: 1-12**

### *መግቢያ*

- በፍፁም መራመድ የማይችለውን ምግብን ጨምሮ ለመኖር የሚያስፈልጉትን ነገሮች ለማግኘት በልመና ስለ ተሰማራው ሽባ ሰው በሚገባ አስረዷቸው።
- ለዚህም ይረዳችሁ ዘንድ ክራች (ምርኩዝ) ልታሳዩቸው ትችላላችሁ። ሆኖም ይህ ሰው የሚንቀሳቀሰው ምርኩዝ ተጠቅሞ ሳይሆን ጓደኞቹ እየተሸከሙት እንደሆ አስረዷቸው።
- ሰውዬውን የሚወክል የኀዘንተኛ ፊት ስዕል ስሩ።

### የማስተማር ጊዜ

- አንድ ቀን ጴጥሮስና ዮሐንስ ወደ መቅደስ ሊገቡ ሲሉ ይህ ሰው ሳንቲም እንዲሰጡት ለመናቸው።. (**የሐዋርያት *ሥራ*** 3: 1–5) *አጠገቡ ለጥቂት ጊዜ ቆም ብለው እንደነበር ንገሯቸው።*
- የጴጥሮስን ቃላት ተጠቀሙ። "ወርቅ ወይንም ብር የለኝም። ያለኝን ግን አስጥሃለሁ። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተነስተህ ተራመድ።" (**የሐዋርያት *ሥራ*** 3: 6–7*) ብርና ወርቅ ለጥቂት ጊዜ ብቻ ልንጠቀምባቸው የምንችላቸው ነገሮች እንደሆነ አብራሩላቸው። የሰውን የተጎዳ አካል ማስተካከል አይችሉም።* ጴጥሮስ የሰውዬውን ሕይወት ሙሉ በሙሉ የሚለውጥ ነገር አቀረበለት።
- ጴጥሮስ እጁን ይዞ አስነሳው። በድንገትም የሰውዬው አግሮች በረቱ። በሕይወቱ ለመጀሪያ ጊዜ መራመድና መዝለል ቻለ። እግዚአብሔርን ማመስገኑን ማቋረጥ አልቻለም። ከጴጥሮስና ከዮሐንስ ጋርም እግዚአብሔርን እያመሰገነ አብሮ ወደ መቅደስ ገባ። (**የሐዋርያት *ሥራ*** 3: 8) *አሁን ደግሞ ቀደም ብላችሁ ከሳላችሁት የኀዘንተኛ ፊት ጋር የሚነፃፀር ደስተኛ ፊት አሳዮቸው። ሽባው ሰው በየእለቱ በመቅደስ ደጅ ላይ ተቀምጦ ሲለምን ብታዩት ምን ታስባላችሁ?*
- በሆነው ነገር ሁሉም ሰው ተደነቀ። (**የሐዋርያት *ሥራ*** 3: 9–12)
- *የጴጥሮስን አብነት እንዴት መከተል እንደምንችል አስቡ። ሰዎችን በተጨባጭ መርዳት ስለ ምንችልባቸው መንገዶች አውሩ። ለሌሎች ልንሰጣቸው የሚገባ ዋነኛ ስጦታ የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስን የምስራች መንገር መሆኑን ጥቀሱላቸው።*
- *ልክ እንደዚህ ሽባ ሰው እኛም በሕይወታችን ችግሮች አሉብን። የኢየሱስ ክርስቶስ ኃይል ልክ መራመድ የማይችለውን ሽባ ሸው ችግር አሰውግዶ እንዲራመድ እንዳስቻለው የእኛንም ኃጢአት ማስወገድ ይችላል።*
- *እግዚአብሔርን ልናመሰግንባቸው የሚገቡ አንዳንድ ነገሮች አስቡ።*

**የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን አጠናቁ።**

### የመማር ጊዜ

ቁልፍ ጥቅሱን እንደአሰፍላጊነቱ አስተምሩ፣ አብራሩ። - **ደረጃ 1 - የሐዋርያት *ሥራ* 3: 6, ደረጃ 2 - የሐዋርያት *ሥራ* 3: 16.** አስፈላጊ ከሆነ ልጆች እየተራመዱ፣ እየዘለሉ፣ እንጣጥ እያሉ ቁልፍ ጥቅሱን እንዲናገሩ ማድረግ ይቻላል።

### የክለሳ ጊዜ

- ስንት ሰዓት ነበር?
- ጴጥሮስና ዮሐንስ የሚሄዱት የት ነበር?
- ሽባው ለምን ያህል ጊዜ ነው መራመድ ያልቻለው?
- በየእለቱ የት ይቀመጥ ነበር?
- ጴጥሮስንና ዮሐንስን የለመናቸው ምን ነበር?
- ጴጥሮስ ሽባውን ለመፈወስ የተጠቀመበት ስም የማንን ስም ነበር?
- ሽባወን በተጨማሪ ምን አለው?
- አሁን ሽባው ሰው ማድረግ የቻላቸው ሶስት ነገሮች ምንድናቸው?
- ከተፈወሰ በኋላ ወዴት ሄደ?
- የኢየሱስ ኃይል በሕይወታችን ምን ማድረግ ይችላል?

*<u>ሀ7 ታሪክ 3</u>*

**ጴጥሮስ በወህኒ ቤት – ይህ ታሪክ እግዚአብሔር የሚያገለግሉትን እንዴት እንደሚረዳቸው የሚያሳይ ታሪክ ነው።**

**በዚህ ክፍል የምንማራቸው  የሚከተሉትን ነው።**

- የመጀመሪያዎቹ ክርስቲያኖች ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ከሰቀሉት የኃይማኖት መሪዎች በኩል ከፍተኛ ተቃውሞ ገጥሟቸው እንደነበር እንማራለን።
- ኢየሱስን በእውነት የሚወዱት በምንም አይነት ችግር ውስጥ ቢያልፉም ይታዘዙታል።

**ቁልፍ ጥቅስ** **ዕብራውያን 13: 6**
**የጥናት ክፍል :** **የሐዋርያት *ሥራ* 4: 1-22**

### *መግቢያ*

- ይህ ታሪክ ያለፈው ታሪክ ተከታይ እንደመሆኑ አንዳንድ መሠረታዊ እውነቶችን መለስ ብሎ ማየት መልካም ነው።
- ከዚህ በፊት የተጠቀማችሁበትን የኃዘንተኛና የደስተኛ ፊት ስዕሎችን አሁን ተጠቀሙባቸው።
- ሽባው ሰው እንዴት ነበር መራመድ የቻለው? ልጆች ይህ ሰው የተራመደው በኢየሱስ ኃይል እንደሆነ መረዳታቸውን አረጋግጡ።

### የማስተማር ጊዜ

- ከዚህ በኋላ ጴጥሮስና ዮሐንስ ስለ ተነሳው ኢየሱስ ሰበኩ። ብዙ ሰዎችም በስብከታቸው አመኑ። (**የሐዋርያት *ሥራ* 4: 1–2, 4**) ሆኖም የቤተ መቅደሱ ኃላፊዎች እጅግ ተቆጡ። ጴጥሮስንና ዮሐንስን አስረው ወህኒ አስገቧቸው። (**የሐዋርያት *ሥራ* 4: 3**) *ይህ ምን እንደሚመስል አስረዷቸው።*
- በሚቀጥለው ቀን ወደ ፍርድቤት ለምርመራ ቀረቡ። (**የሐዋርያት *ሥራ* 4: 5–7**) *ፍርድ ቤት ማለት ዳኞች ያሉበትና አንድ ሰው ያደረገው ድርጊት ትክክል መሆን አለመሆኑ የሚወሰንበት ስፍራ መሆኑን ንገሯቸው።*
- እንደገናም ጴጥሮስ በመንፈስ ቅዱስ ተረድቶ ሽባው ሰው እንዴት እንደተፈወሰ አስረዳቸው። (**የሐዋርያት *ሥራ* 4: 8–12**) የፍርድ ሸንጎውም በእነጴጥሮስ ላይ ምን አይነት ውሳኔ ማስተላለፍ እንዳለበት ግራ ተጋባ። ትልቅ ተአምር እንደሆነ አውቀዋል። ከብዙ ውይይት በኋላ ጴጥሮስና ዮሐንስ ደግመው ስለ ኢየሱስ እንዳይናገሩ አዘዟቸው። (**የሐዋርያት *ሥራ* 4: 13–19**) *ጴጥሮስና ዮሐንስ ስለዚህ ምን ይሰማቸዋል? ትዕዛዙን ያከብሩት ይሆን?*
- ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ አለመናገር በጣም ከባድ እንደሆነ ጴጥሮስና ዮሐንስ ያውቃሉ! (**የሐዋርያት *ሥራ* 4: 20**) *ኢየሱስ ክርስቶስን እጅግ በጣም ያፈቅሩት ስለ ነበረ ሊታዘዙት ፈቀዱ። ምንም ቢፈጠር ኢየሱስ ከአጠገባቸው እንደማይለይ ያውቁ ነበር። መንፈስ ቅዱስ እንደሚረዳቸው እርግጠኞች ነበሩ።*
- *በምንም አይነት ሁኔታ ውስጥ እንለፍ ኢየሱስ እኛም እንድንታዘዘውና እንድንወደው ይፈልጋል።*

**የዘመኑ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን አጠናቁ።**

### የመማር ጊዜ

ቁልፍ ጥቅሱን እንደአስፈላጊነቱ አስተምሩ፣ አብራሩ። - **ዕብራውያን** 13: 6. በገመድ የመስቀል ጨዋታን ለመጀመሪያዎቹ 5 ቃላትና ለማጣቀሻው መጫወት ትችላላችሁ። ይህም ተከታዮቹን ሁለት ክፍሎች ከመጨመራችሁ በፊት የምታደርጉት ይሁን። ልጆች በሶስት ቡድኖች ይከፈሉና እያንዳንዳቸው አንዱን ክፍል ይሉታል። ማጣቀሻውንም መድገም ይችላሉ። *እነኝህ ቃላት ለጴጥሮስና ለዮሐንስ ይጠቅሟቸው ነበር ብላችሁ ታስባላችሁ? እኛም እነኝህን ቃላት ማወቃችን በጣም እንደሚጠቅመን አስረዷቸው።*

### የክለሳ ጊዜ

- የሚከተሉት ጥያቄዎች እውነት ወይንም ሐሰት በማለት የሚመለሱ ጥያቄዎች ናቸው። ጥያቄዎቹ በካርድ ላይ ተፅፈው በከረጢት ውስጥ እንዲቀመጡ ይደረጋል። እያንዳንዱ ጥያቄ በላዩ ላይ ቁጥሮች ተፅፈውበታል። እነኝህ ቁጥሮችም ከ 5 – 100 የሚደርሱ ቁጥሮች ናቸው። ሁለት ቡድኖችን መስርቱ።
- ፖሊሶቹ በጴጥሮስና በዮሐንስ ላይ እጅግ ተቆጥተው ነበር።
- በወህኒ አንድ ሌሊት አሳልፈዋል።
- ከእስር ቤት ሲለቀቁ ፍርድ ቤት ቀርበው ምርመራ ተካሄደባቸው።
- ጴጥሮስ ሽባውን ሰው ያዳነው የኢየሱስ ኃይል እንደሆነ በፍርድ ቤቱ ለነበሩት ተናገረ።
- መንፈስ ቅዱስ ጴጥሮስና ዮሐንስ በፍርድ ቤት ውስጥ መናገር እንዲችሉ ረዳቸው።
- ጴጥሮስና ዮሐንስ ከፍርድ ቤት አመለጡ።
- ፍርድ ቤቱ ጴጥሮስና ዮሐንስ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዳይናገሩ ወሰነባቸው።
- ጴጥሮስና ዮሐንስም የፍርድ ቤቱን ትዕዛዝ ለማክበር ተስማሙ።

## ሀገ ታሪክ 4

**ጴጥሮስ ነፃ ወጣ። – ይህ ታሪክ እግዚአብሔር ፀሎትን እንደሚመልስ የሚናገር ታሪክ ነው።**

| | |
|---|---|
| | **በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>• እግዚአብሔር ኃይሉን ለክርስቲያኖች በመስጠትና በማገዝ ስራውን እንዲያከናውኑ ያደርጋቸዋል።<br>• በሚገጥሙን በማናቸውም ሁኔታዎች ፀሎት እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው።<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ** **የሐዋርያት ሥራ** 4: 31 **ወይንም ማቴዎስ** 6: 33<br>**የጥናት ክፍል :** **የሐዋርያት ሥራ** 4: 23-31 |
| መግቢያ | ልጆች ለጓደኞቻቸው ወይንም ለቤተ ሰቦቻቸው አባላት ማካፈል ስለ ሚፈልጉት ዜና አውሩ። ምናልባትም ይህ ዜና በውድድር ስለ ማሸነፍ ወይንም አስደሳች ስለሆነ ሽርሽር ሊሆን ይችላል። ወይንም ደግሞ አንድ አስጨናቂ ጉዳይ ገጥሟቸው ጉዳዩን ለጓደኞቻቸው ከነገሯቸው በኋላ መፍትሔ ስለ ማግኘታቸው ሊሆን ይችላል። |
| የማስተማር ጊዜ | • ጴጥሮስና ዮሐንስ ለወዳጆቻቸው ሊነግሯቸው የሚገባ ዜና ነበራቸው። (**የሐዋርያት ሥራ** 4: 23) ይህም መልካም ዜና ከወህኒ መፈታታቸው ሲሆን ደስ የማያሰኘው ዜና ደግሞ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዳይናገሩ መታዘዛቸው ነው።<br>• የጴጥሮስና የዮሐንስ ወዳጆች ትክክለኛ ውሳኔ ወሰኑ። እርሱም በጉዳዩ ላይ መፀለይ ነው። (**የሐዋርያት ሥራ** 4: 24-30) ሁሉም ነገር ከእግዚአብሔር ቁጥጥር በታች እንደሆነ ያውቃሉ። ስለ ኢየሱስ እንዳይናገሩ ካዘዟቸው ሰዎች ይልቅ እግዚአብሔር ብርቱ እንደሆነ ተረድተዋል። እየፀለዩም እግዚአብሔር ስላደረጋቸውና የእርሱን ኃይል ስለ ሚያሳዩ ድንቅ ነገሮች ያስቡ ነበር። በኢየሱስ ኃይል ሌሎች ታላላቅ ተአምራትን እንዲያደርጉ እንዲሁም እንዲያበረታቸው እግዚአብሔርን በፀሎት ለመኑት። (**የሐዋርያት ሥራ** 4: 29,30)<br>• ልክ ፀሎታቸውን እንደጨረሱ እግዚአብሔር መልስ ሰጣቸው! (**የሐዋርያት ሥራ** 4: 31) *የነበሩበት ስፍራ ተናወጠ። ምክንያቱም መንፈስ ቅዱስ ከእነርሱ ጋር በመሆን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ በሚናገሩበት ጊዜ እንደሚረዳቸው ማረጋገጫ መሆኑን አስረዷቸው።*<br>• *አስቸጋሪ ነገሮች ሲገጥሙን ወደ እግዚአብሔር መፀለይ ተገቢ መሆኑን አስረዷቸው።*<br>• *እግዚአብሔር ፀሎታችንን ሰምቶ ይመልሳል። ልክ በታሪኩ ውስጠ እንዳየናቸው ሰዎችም ጌታ ኢየሱስን በሕይወታችን አንደኛ ለማድረግ ይረዳናል።*<br>• *ከደረጃ 2 ተማሪዎች ጋር ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ በፍፁም እንዳይነገር በሚከለከልበት አካባቢ ስለ ሚኖሩ ክርስቲያኖች ጋር መነጋገር ትችላላችሁ። እነኝህ ክርስቲያኖች ኢየሱስ ክርስቶስን አንደኛ ማድረግ የሚችሉበትን ብርታት እግዚአብሔር እንዲሰጣቸው ልንፀልይላቸው ይገባናል።*<br><br>**የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን አጠናቁ።** |
| የመማር ጊዜ | ቁልፍ ጥቅሱን እንደአስፈላጊነቱ አስተምሩ፣ አብራሩ። - **የሐዋርያት ሥራ** 4: 31 **ወይንም ማቴዎስ** 6: 33. **በማቴዎስ** 6: 33, "ፈልጉ" የሚለው ቃል ትርጉም ማስቀመጥ ማለት ነው። የእግዚአብሔር መንግስት ማለት ጌታ ኢየሱስን ጨምሮ ለእግዚአብሔር አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን ሁሉ ይጠቀልላል። |
| የክለሳ ጊዜ | የሚከተለው መልመጃ በሀገ ውስጥ ባሉት ታሪኮች ላይ የተመሠረተ ነው።<br><br>• የኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ ለምንድነው መንፈስ ቅዱስ የሚያስፈልጋቸው?<br>• መንፈስ ቅዱስ ሲመጣ ለደቀ መዛሙርቱ ያዩት ምን ነበር?<br>• ይህን ቁልፍ ጥቅስ አሟሉት።<br>• "እንግዲህ ይህን እናንተ የሰቀላችሁትን ኢየሱስን እግዚአብሔር __________________ ______________ክርስቶስም እንዳደረገው የእስራኤል ወገን ሁሉ በእርግጥ ይወቅ።" (**የሐዋርያት ሥራ** 2: 36) [ታሪክ 1]<br>• በቤተ መቅደስ ደጃፍ ላይ ይቀመጥ የነበረው ሰው የሚለምነው ለምን ነበር?<br>• ለምን ያህል ጊዜ ነበር መራመድ የማይችለው?<br>• በዚህ ቁልፍ ጥቅስ ውስጥ የጎደሉትን ቃላት አሟሉ። "በናዝሬቱ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ______ ____ ______ ______።"<br>• ይህ ተዓምር ለሕዝቡ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ያረጋገጠላቸው ነገር ምን ነበር?<br>• ጴጥሮስና ዮሐንስ የታሰሩት ለምን ነበር?<br>• ጴጥሮስና ዮሐንስ ምን እንዳያደርጉ ነው ፍርድ ቤቱ ያዘዛቸው?<br>• እግዚአብሔር የጴጥሮስና የዮሐንስ ወዳጆችን ፀሎት ሲመልስ ምን ሆነ? |

<u>ሀ8 ታሪክ 1</u>

**ጴጥሮስ ዶርቃን ረዳት። - ይህ ታሪክ ዶርቃ ከሙታን ሰለመነሳቷ የሚናገር ታሪክ ነው።**

| | |
|---|---|
| | **በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>• ዶርቃ ስትፈወስ የኢየሱስ ኃይል በስራ ላይ ነበር።<br>• በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ምላሽ መስጠት ይገባናል።<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ** **የሐዋርያት ሥራ 9: 42**<br>**የጥናት ክፍል :** **የሐዋርያት ሥራ 9: 32-43** |
| *መግቢያ* | • *ያለንን በማካፈል ልንረዳቸው ስለ ምንችል ሰዎች ተነጋገሩ። ይህን ለማብራራት ምናልባትም ቪዥዋል (የእይታ) መርጃ መሳሪያዎችን መጠቀም ትችላላችሁ።*<br>• *ዶርቃ ጌታ ኢየሱስን የምትወድ ደግ ሴት እንደነበረች ንገሯቸው። አብዛኛውን ጊዜዋን የምታሳልፈው ሌሎችን በመርዳት ነበር። በተለይም ለተቸገሩ ልብስ በመስፋትና በማዘጋጀት ትረዳቸው ነበር።* |
| የማስተማር ጊዜ | • አንድ ቀን ዶርቃ በጣም ስለ ታመመች ሞተች። (**የሐዋርያት ሥራ 9: 37**) *ወዳጆቿ ምን ተሰምቷቸው ይሆን?*<br>• ሁለት ክርስቲያኖች ኢዮጴ በምትባል አጎራባች ከተማ የሚገኘውን ጴጥሮስን ፍለጋ ሄዱ። (**የሐዋርያት ሥራ 9: 38, 39**)<br>• ጴጥሮስም በቀጥታ ወደ ዶርቃስ ቤት ሄዱ። (Acts: 9: 40, 41) *ጴጥሮስ መጀመሪያ እንዴት እንደፀለየ፣ እንዴት እንደተናገራት፣ እጇን ይዞ በእግሮቿ እንድትቆም እንዴት እንደረዳት በዝርዝር ንገሯቸው። ዶርቃ ሕያው ሆነች! ጴጥሮስ በዶርቃስ ቤት ሲደርስ የነበረውን የሐዘን ድባብ አሁን ካለው የደስታ ስሜት ጋር አወዳድሩት። ጴጥሮስ ይህን ተአምር ማድረግ የቻለው የኢየሱስ ክርስቶስ ኃይል በእርሱ አልፎ ይሰራ እንደነበር በአፅንኦት ንገሯቸው።*<br>• ብዙ ሰዎች በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ አመኑ። (**የሐዋርያት ሥራ 9: 42**)<br>• *ልክ ዶርቃ ሕያው ስትሆን በማየታቸው በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እንዳመኑት ሰዎች እኛም በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ልናምን ይገባናል።*<br>• *ይህ ምን ማለት እንደሆነ በቀላሉ አስረዷቸው። ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው። ኃጢአታችንን ማስወገድ ይችላል። እንዲሁም ሕያው ነው። በኢየሱስ ማመን ማለት ሙሉ በሙሉ በእርሱ መደገፍ ማለት ነው።*<br><br>**የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን አጠናቁ።** |
| *የመማር ጊዜ* | ቁልፍ ጥቅሱን አስተምሩ። - **የሐዋርያት ሥራ 9: 42**<br>*ይህ ቁልፍ ጥቅስ ለትንንሽ ልጆች ሳይቀር ቀላል ነው። ልጆች ጥቅሱ እንደገባቸው አረጋግጡ። "ብዙ ሰዎች" የሚለውን ሀሳብ መረዳታቸውን አረጋግጡ። በኢየሱስ እንዲያምኑ ያደረጋቸው ምንድነው? በኢየሱስ ማመን ለእኛ ለምን ያስፈልገናል? አንድ ሰው በክርስቶስ እንዴት ማመን ይችላል?* |
| የክለሳ ጊዜ | • ዶርቃ የምትኖረው የት ነበር?<br>• ሰዎችን የምትረዳው እንዴት ነበር?<br>• ዶርቃ ስትሞት ሰዎች ምን ተሰማቸው?<br>• ጴጥሮስን ፍለጋ የሄዱት እነማን ነበሩ?<br>• ጴጥሮስ በዶርቃ አልጋ አጠገብ ተንበርክኮ ምን አደረገ?<br>• ጴጥሮስ ለዶርቃ ምን ብሎ ተናገራት?<br>• ጴጥሮስ ዶርቃን ከተናገራት በኋላ ምን አደረገ?<br>• ዶርቃ ሕያው ስትሆን ብዙ ሰዎች ምን አደረጉ?<br>• ቁልፍ ጥቅሱ ያለው የት ነው? |

<u>ሀ8 ታሪክ 2</u>

**የጴጥሮስ ራዕይ – ይህ ታሪክ እግዚአብሔር ሁሉንም ሰዎች እንደሚያፈቅር የሚያሳይ ታሪክ ነው።**

| | |
|---|---|
| | **በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው፡፡**<br>• ጴጥሮስ እግዚአብሔር እንዲያደርግ የፈለገውን ለማድረግና ለመታዘዝ ፈቃደኛ እንደነበር እንማራለን።<br>• እግዚአብሔር ሁሉንም ሰዎች ይወዳል። እንዲሁም ሁሉም ሰዎች ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ መልካሙን ዜና እንዲሰሙ እንደሚፈልግ እንማራለን።<br>**ቁልፍ ጥቅስ** **ዮሐንስ** 3: 16<br>**የጥናት ክፍል :** **የሐዋርያት ሥራ** 10: 9-23 |
| *መግቢያ* | • ከተለያዩ አካባቢዎች የመጡ ሰዎች ልዩነት እንዳላቸው አውሩ። ከተገኘም ፎቶዎችን አሳዮቸው።<br>• የቆዳ ቀለም፣ የፀጉር፣ የአለባበስ፣ የቋንቋ ወዘተ... ልዩነቶችን አውሩ።<br>• እግዚብሔር ሁሉንም ሕዝቦች ፈጠረ። ሁሉም ሰዎች እግዚአብሔርንና ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን እንዲያውቁ ይፈልጋል። |
| የማስተማር ጊዜ | • ጴጥሮስ በኢዮጴ በመፀለይ ላይ ሳለ እግዚአብሔር ሁሉንም ሰዎች እንደሚወድ አስተማረው። (ይህን ታሪክ ሀ8 ታሪክ 1 ጋር አዛምዱት።) (**የሐዋርያት ሥራ** 10: 9–16) *ወደ ራዕዩ ዝርዝር መሄድ አያስፈልግም። ከደረጃ 2 ልጆች ጋር ለጴጥሮስ ለምን ይህ ከባድ ሊሆንበት እንደሚችል መነጋገር ትችላላችሁ። ጴጥሮስ አይሁዳዊ ነበር። ለእግዚአብሔርም ምርጥ ሕዝቦቹ አይሁዳውያን ብቻ እንደሆኑ ያምን ነበር። ጴጥሮስ ሁሉም ሰዎች ለእግዚአብሔር ልዩ እንደሆኑ መማር ነበረበት።*<br>• ሶስት ሰዎች ጴጥሮስ ወዳለበት መጥተው ወደ ቆርኔሌዎስ ቤት አብሯቸው እንዲሄድ ጠየቁት። (**የሐዋርያት ሥራ** 10: 17–22) *ቆርኔሌዎስ በጣም ተፈላጊ የሮማን ወታደር እንደነበረና ስለ እግዚአብሔር የበለጠ ለማወቅ የሚሻ ሰው እንደነበረ አስረዷቸው። ቆርኔሌዎስ ከጴጥሮስ እጅግ በጣም ይለይ ነበር። ጴጥሮስ ደግሞ እንደቆርኔሌዎስ አይነት ሰዎች አጠገብ ድርሽ አይልም ነበር። ጴጥሮስ ወደ ቆርኔሌዎስ ቤት መሄድ ትክክለኛ ነገር መሆኑን ያወቀው እንዴት እንደነበር አስረዷቸው። ለዚህም (1) እግዚአብሔር ምን አስተማረው? (2) መንፈስ ቅዱስ እንዴት መራው?*<br>• ጴጥሮስ የቆርኔሌዎስ መኖሪያ ከተማ ወደ ሆነው ወደ ቂሳሪያ ተጓዘ። (60 ኪ.ሜ ያህል ይርቃል።) (**የሐዋርያት ሥራ** 10: 23) *ይህን ርቀት ልጆቹ መረዳት እንዲችሉ አንድ የሚያውቁትን አካባቢ ንገሯቸው። ይህ ጉዞ አንድ ሙሉ ቀን ሊወስድ የሚችል ጉዞ ነው። ጴጥሮስ ይህን ጉዞ ለማድረግ ሲወስን ለእግዚአብሔር ታዞ እንደሆነ በትኩረት ንገሯቸው።*<br>• *እግዚአብሔር ሁሉም ሰው በእግዚአብሔር እንደሚወደድ እንዲያውቁ እንደሚፈልግ በአፅንኦት ንገሯቸው። ሰዎች ሁሉ የኃጢአት ይቅርታ ማግኘት ይችሉ ዘንድ እግዚአብሔር ልጁን በመስቀል ላይ እንዲሞት አሳልፎ ሰጥቶታል።*<br>• *ጌታ ኢየሱስን የምታውቁት ከሆነ ሌሎች ጌታ ኢየሱስን እንዲያውቁት ማድረግ አለባችሁ።*<br><br>**የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን አጠናቁ።** |
| *የመማር ጊዜ* | ቁልፍ ጥቅሱን እንደአስፈላጊነቱ አስተምሩ፣ አብራሩ። - **ዮሐንስ** 3: 16 |
| የክለሳ ጊዜ | • ጴጥሮስ የሚኖረው ከማን ጋር ነበር?<br>• ጴጥሮስ በእኩለ ቀን ምን ያደርግ ነበር?<br>• እግዚአብሔር ከጴጥሮስ ጋር ሲነጋገር ጴጥሮስ ምን እንዲያውቅ ፈለገ?<br>• ጴጥሮስን ለማየት የመጡት ስንት ሰዎች ነበሩ?<br>• ጴጥሮስ የሚገበኘው ማንን ነበር?<br>• የቆርኔሌዎስ ስራ ምን ነበር?<br>• ጴጥሮስ ወደ ቆርኔሌዎስ ቤት የሄደው ለምን ነበር?<br>• እግዚአብሔር በአለም ውስጠ ያሉትን ሰዎች በሙሉ መውደዱን የገለፀው እንዴት ነበር?<br><br>**ተውኑት :** ጎብኚዎቹ ጴጥሮስ ወዳለበት ቤት ሲደርሱ የሚያሳይ ድራማ ማዘጋጀት ይቻላል። ይህንንም በታሪክ ሶስት እንዲቀጥል ማድረግ ይቻላል። አዋቂዎች የጎብኚዎችንና የጴጥሮስን ገፀ ባሕርያት መጫወት ይችላሉ። |

## ሀ8 ታሪክ 3

**ጴጥሮስና ቆርኔሌዎስ – ይህ ታሪክ አንድ ሮማዊ ወታደር እግዚአብሔር ስላዳነው የሚናገር ታሪክ ነው።**

| | |
|---|---|
| | **በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>• ቆርኔሌዎስ በጌታ ኢየሱስ ካመኑና አይሁዳዊ ካልሆኑ የመጀመሪያዎቹ ሰዎች መካከል አንደኛው ሲሆን እንዴት በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እንዳመነ እንማራለን።<br>• በኢየሱስ የሚያምኑ ሰዎችን ኃጢአት እግዚአብሔር ይቅር እንደሚል እንማራለን።<br>**ቁልፍ ጥቅስ** **የሐዋርያት** ***ሥራ*** 10: 43<br>**የጥናት ክፍል :** **የሐዋርያት** ***ሥራ*** 10: 23-48 |
| *መግቢያ* | • ይህ ያለፈው ትምህርት ተከታይ እንደመሆኑ መጠን አንዳንድ ዝርዝሮችን ለመከለስ ያመቻችሁ ዘንድ በታሪክ 2 ውስጥ ያሉ ጥያቄዎችን መጠቀሙ ተገቢነት ይኖረዋል።<br>• ይህን ካደረጋችሁ በኋላ በአካባቢያችሁ ብዙ ሰዎች በአንድ ላይ የሚሰበሰቡበትና መልካሙን ዜና እንዲሰሙ የሚደረግበትን አንድ ትልቅ ክንዋኔ እንደምሳሌ ንገሯቸው። |
| የማስተማር ጊዜ | • ጴጥሮስ ወደ ቆርኔሌዎስ ቤት ደረሰ። (**የሐዋርያት** ***ሥራ*** 10: 24–33) ጴጥሮስ በዚያ እንደደረሰ ያለውን ትዕይንት በስዕላዊ መልኩ ለልጆች ለማሳየት ሞክሩ። ይህም የቆርኔሌዎስ ቤት በቤተሰቡ አባላት፣ በወዳጆቹ፣ እንዲሁም ጴጥሮስን ለማየት ጉጉት ኖሯቸው በዚያ የተሰበሰቡትን ሰዎች ማየት የሚያስችል ስዕላዊ መግለጫ መሆን አለበት። ቆርኔሌዎስ ጴጥሮስን እንደ አንድ የክብር እንግዳ ልዩ አቀባበል ሊያደርግለት አሰበ። ስለዚህም ወደ መሬት ለጥ ብሎ ሰገደለት! ጴጥሮስም እንዲነሳ አዘዘው። ምክንያቱም ለተራ ሰው መስገድ ተገቢ ስላልሆነ ነው። ከዚያም ቆርኔሌዎስ ጴጥሮስን ልኮ እንዲያስመጣው በእግዚአብሔር እንደታዘዘ ነገረው። *እግዚአብሔር ሁለቱንም ሰዎች ለዚህ ግንኙነት ሲያዘጋጃቸው እንደነበረ ልትነግሯቸው ትችላላችሁ።*<br>• የጴጥሮስ መልእክት (**የሐዋርያት** ***ሥራ*** 10: 34–43) *እግዚአብሔር ከሁሉም ነገዶችና ቋንቋዎች ሰዎች በኢየሱስ እንዲያምኑ እንደሚፈልግ ጴጥሮስ በዚያ ተሰብስበው ለነበሩት ሰዎች እንዴት እንደነገራቸው አስረዷቸው።*<br>• ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ጴጥሮስ ለተሰበሰቡት ሰዎች የነገራቸውን እውነታዎች ተወያዩባቸው። - ያደረጋቸውን መልካም ነገሮች፣ ሰዎችን ስለ መፈወሱ፣ እንደሞተና እግዚአብሔር ከሙታን እንዳስነሳው ወዘተ... ጌታ ኢየሱስ አንድ ቀን ፈራጅ ሆኖ እንደሚገለጥ ከሁሉም በላይ ደግሞ በእርሱ የሚያምኑትን ያኃጢአት ይቅርታ እንደሚሰጣቸው ነገሯቸው።<br>• የአድማጮቹ ምላሽ። (**የሐዋርያት** ***ሥራ*** 10: 44–48) መንፈስ ቅዱስ የተሰበሰቡት ሰዎች ጴጥሮስ እየተናገረ ያለውን ነገር እንዲያስተውሉ ረዳቸው። በኢየሱስ ክርስቶስ አመኑ። የኃጢአት ይቅርታንም አገኙ።<br>• *እኛም ልክ እንደነኝህ ሰዎች የኢየሱስ ክርስቶስን መልካም ዜና ስንሰማ እርሱን ማመን እንደሚገባን አስረዷቸው። እኛም የኃጢአት ይቅርታን እናገኛለን።*<br><br>**የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን አጠናቁ።** |
| *የመማር ጊዜ* | ቁልፍ ጥቅሱን እንደአስፈላጊነቱ አስተምሩ፣ አብራሩ። - **የሐዋርያት** ***ሥራ*** 10: 43. *"በእርሱ የሚያምን ሁሉ" እና "የኃጢአት ስርየት" የሚሉትን ሐሳቦች አብራሩላቸው።* |
| የከለሳ ጊዜ | ከመልመጃ ጥያቄዎች ይልቅ በትልቁ በተገፈ ቁልፍ ጥቅስ ዙሪያ የተለያዩ የሰው ፊት ስዕሎች ተቆራርጠው የተለጣጠፉበት ኮላዥ አዘጋጁ። እያንዳንዱ ልጅ የራሱን የፊት ሥዕል መሳል ይችላል። ይህ ጴጥሮስ ስለ እግዚአብሔር ፍቅር የገባውን እውነት አጠናከረን ለልጆቹ የምናሳይበት መንገድ ነው። "በእርሱ የሚያምን ሁሉ" የሚለው ሀሳብም እያንዳንዳቸውን በግል እንደሚጨምር እንዲያስተውሉ ይረዳቸዋል። በአማራጭም ልጆች ካረጁ ጋዜጦች ላይ የሰው ፊቶችን ቆራረጠው ማውጣት ይችላሉ።<br>**ተውኑት** : በታሪክ 2 እንደተጠቀሰው ይህ ታሪክም በድራማ መልክ መቅረብ ይችላል። |

## <u>ሀ8 ታሪክ 4</u>

## ጴጥሮስ ዳነ። – ይህ  ታሪክ እግዚአብሔር ፀሎትን እንደሚመልስ የሚያሳይ ታሪክ ነው።

**በዚህ ክፍል የምንማራቸው  የሚከተሉትን ነው።**

- የጴጥሮስ ወዳጆች ለጴጥሮስ እንደፀለዩለት እንማራለን።
- እግዚአብሔር የፀሎታችንን መልስ በድንቅና በተአምር መመለስ ይችላል።

**ቁልፍ ጥቅስ** **ያዕቆብ 5: 16**
**የጥናት ክፍል :** ***የሐዋርያት ሥራ* 12: 1-19**

### *መግቢያ*

- ከጓደኞቻችን ጋር ለመገናኘት ወይንም አንድ አስፈላጊ ነገር ለመጠየቅ ስልክ መጠቀም እንደምንችል ለልጆች ንገሯቸው። የምትችሉ ከሆነም የሞባይል ስልክ እንደ ትምህርት መርጃ አድርጋችሁ ተጠቀሙ።
- ፀሎት ማለት ከእግዚአብሔር ጋር የምንነጋገርበት መሳሪያ መሆኑን አስረዷቸው። እግዚአብሔር መልሶ አይናገረም። ሆኖም ግን ሁልጊዜ ያደምጠናል። ፀሎታችንን የመመለስ ስልጣን አለው።
- ይህ ታሪክ በአንድ እጅግ በጣም አስፈላጊ በሆነ ጉዳይ ላይ ሲፀልዩ ስለ ነበሩ ሰዎች የሚናገር ታሪክ ነው።

### የማስተማር ጊዜ

- ጴጥሮስ በወህኒ ቤት ነበር። (**የሐዋርያት *ሥራ* 12: 1–4**) ንጉስ ሄሮድስ የኢየሱስን ተከታዮች እጅግ በጣም ይጠላቸው ነበር። ያዕቆብን አስገድሎት ነበር። ያዕቆብ ከሞተ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ጴጥሮስን ደግሞ አስይዞ ወደ ወህኒ ቤት አስገባው። ከዚህ በፊት ጴጥሮስ ታስሮ እንደነበር አስታውሱ። (**የሐዋርያት *ሥራ* 5:  ሀ7/ ታሪክ 3**)
- የጴጥሮስ ወዳጆች ፀሎት ጀመሩ። (**የሐዋርያት *ሥራ* 12: 5**) *ይህን ማድረግ ለምን ከሁሉም የተሻለ እንደሆነ ተወያዩበት።*
- *ከእስር ነፃ ወጣ።* (**የሐዋርያት *ሥራ* 12: 6-10**) ይህ የሆነው ጴጥሮስ እንደነገ ፍርድ ቤት ሊቀርብ ዛሬ ሌሊት ላይ ነው። *(የዚህ ፍርድ ሂደት ውጤት ምን ያህል ወሳኝ እንደሆነ አስረዷቸው።)* ጴጥሮስ ከሚጠብቁት ከሁለት ወታደሮች ጋር አብሮ ታስሮ ነበር። ከባድ እንቅልፍልም ወስዶት ነበር።  ጴጥሮስን እንዴት የእግዚአብሔር መልአክ በሚያስገርም ሁኔታ ከወህኒ ነፃ እንዳወጣው በድራማና በውስጣቸው መገረም እስኪሞላባቸው ድረስ በዝርዝር ለልጆች ንገሯቸው። ጴጥሮስ ሕልም የሚያይ ነበር የመሰለው።
- ጴጥሮስ በወዳጆቹ ቤት። ጴጥሮስ ከወህኒው ከወጣ በኋላ በጎዳና መሆኑን ተረዳ። ይሄኔ እግዚአብሔር ከወህኒ መልአኩን ልኮ እንዳወጣው አስተዋለ። *ጴጥሮስ አሁን ምን ሊሰማው ይችላል?* ጴጥሮስ በቀጥታ ያመራው ወደ ወዳጆቹ ቤት ሄደ። (**የሐዋርያት *ሥራ* 12: 11–17**) አገልጋይቱ ሮዳ ጴጥሮስ በሩን ሲያንኳኳ ከመክፈቷ በፊት ምን እንዳደረገችና ምን ስሜት እንዳንፀባረቀች አብራሩላቸው። ወዳጆቹ ተደንቀው ነበር?
- *ወደ እግዚአብሔር እንድንፀልይ የሚያስገድዱንን ሁኔታዎችን በተመለከተ ተወያዩ።  እግዚአብሔር ሁልጊዜም ፀሎታችንን ሰምቶ ለእኛ በሚበጀን መልኩ ይመልሳል።*
- *እግዚአብሔር ፀሎታችንን ሲመልስ ማመስገን እንደሚገባን መርሳት የለብንም።*

**የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን አጠናቁ።**

### የመማር ጊዜ

ቁልፍ ጥቅሱን እንደአስፈላጊነቱ አስተምሩ፣ አብራሩ። - ***ያዕቆብ* 5: 16**  ይህ  ጥቅስ ፀሎታችን ልዩነት ማምጣት እንደሚችል የሚናገር ጥቅስ ነው። እግዚአብሔር የእኛን ፀሎት የእርሱን ስራ ለመስራት ይጠቀምበታል።

### የክለሳ ጊዜ

- ጴጥሮስን ወህኒ ያስገባው ማን ነበር?
- ንጉስ ሄሮድስ የገደለው ማንን ነበር?
- እግዚአብሔር መልአኩን ሲልክ ጴጥሮስ ምን እያደረገ ነበር?
- የጴጥሮስ ወዳጆች በአንድ ላይ የተሰባሰቡት ለምን ነበር?
- መልአኩ ጴጥሮስን ምን እንዲያደርግ አዘዘው?
- ጴጥሮስ በወህኒው ደጅ በኩል የወጣው እንዴት ነበር?
- ጴጥሮስና መልአኩ ከመለያየታቸው በፊት በአንድ ላይ ለምን ያህል ጊዜ ተጓዙ?
- ጴጥሮስ ከወህኒ ከወጣ በኋላ ወዴት ሄደ ?
- በቤቱ በር ላይ ጴጥሮስን የተገናኘው ማን ነበር?
- ሮዳ መጀመሪያ ላይ በሩን መክፈት ያልቻለችው ለምን ነበር?

**ተውኑት :** ጴጥሮስ ከወህኒ የወጣበትን ትዕይንት ልጆች ጥንድ ጥንድ ሆነው በድራማ መልክ መስራት ይችላሉ። አንደኛው ልጅ እንደጴጥሮስ ሌላኛው ደግሞ እንደመልአኩ ሆነው ድራማውን መስራት ይችላሉ። ከልጆቹ ድራማ ጋር በተጓዳኝ መልኩ ደግሞ አንድ አዋቂ ሰው ትረካ መተረክ ይችላል።

**<u>ሀ9 ታሪክ 1</u>**

**ያዕቆብ ወንድሙን አታለል። – ይህ ታሪክ ራስ ወዳድ ስለ መሆን የሚናገር ታሪክ ነው።**

| | |
|---|---|
| | **በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>• ራስ ወዳድነት ማለት ሌሎችን ሰዎች የሚጎዳም ቢሆን እንኳን ራሳችንን ከሁሉም ማስቀደም ማለት እንደሆነ እንማራለን።<br>• እንደያእቆብ ራስ ወዳዶች መሆን እንችላለን። ይህ ደግሞ ኃጢአት ነው።<br>**ቁልፍ ጥቅስ** **ዘፍጥረት 25: 28 ወይም ፊልጵስዩስ 2: 3**<br>**የጥናት ክፍል :** **ዘፍጥረት 25: 19 - 34** |
| መግቢያ | • መንትዮችን ታውቃላችሁ? በስብዕናና በመልክ ይመሳሰላሉ? ከወንድሞቻችሁና ከእህቶቻችሁ ጋር ትደባደባላችሁ?<br>• ራስ ወዳድ መሆን ማለት ምን ማለት ነው? እናንተ የምታውቁትና ራስ ወዳድ ከመሆኑ የተነሳ እናንተን የጎዳችሁ ሰው ትዝ ይላችኋል?<br>• ይህ ታሪክ ምንም መስማማት ሳይችሉ ስለ ቀሩ ሁለት ወንድማማቾች ታሪክ ይናገራል። ከሁለቱ አንደኛው ስለ ራሱ ብቻ የሚያስብ ሲሆን ሌላኛውን ወንድሙን አታለለው። |
| የማስተማር ጊዜ | • ይስሐቅና ርብቃ መንትያ ልጆች እንዲወለዱላቸው ይጠብቁ ነበር። መንትያዎቹ ከመወለዳቸው በፊት ታላቅዬው ታናሽዬውን እንደሚያገለግለው እግዚአብሔር ለርብቃ ነግሯት ነበር። (**ዘፍጥረት** 25: 19-23)<br>• መንትያዎቹ ሲወለዱ እንደሚለያዩ የታወቀ ነገር ነበር። ታላቅዬው ኤሳው ፀጉራማ ነበር። ታናሹ ያዕቆብ ደግሞ ለስላሳ ቆዳ ነበረው። (**ዘፍጥረት** 25: 24-26) እንዲሁም ሁለቱም የሚወዱት ነገር ይለያያል። ኤሳው ጥሩ አዳኝ ነበር። ያዕቆብ ደግሞ ቤት መዋል ያስደስተው ነበር። እናትና አባት ለየቅል የሚወዱት ልጅ ነበራቸው። ይስሐቅ የሚወደው ኤሳውን ሲሆን ርብቃ የምትወደው ደግሞ ያዕቆብን ነበር። (**ዘፍጥረት** 25: 27-28)<br>• አንድ ቀን ያዕቆብ ምግብ እያበሰለ ነበር። ኤሳው ለአደን ወጥቶ ነበር። ልጆች ትዕይንቱን ማየት እንዲችሉ እርዷቸው። – (ኤሳው ተርቧል እንዲሁም ደክሞታል። በመብሰል ላይ ያለው ምግብ መዓዛ።) ነገር ግን ያዕቆብ እጅግ በጣም ሲበዘ ተንኮለኛ ነበር። ፈጥኖም ኤሳው ብኩርናውን ቢሰጠው እርሱም እያበሰለ ካለው ምግብ ሊሰጠው ፈቃደኛ መሆኑን ነገረው። *ብኩርና ምን ማለት እንደሆነ ንገሯቸው። በቤተ ሰብ ውስጥ መጀመሪያ የተወለደ ልጅ የበኩርነት መብት አለው። ይህ ማለትም አባትየው ቢሞት ቤተሰቡን የመምራት ኃላፊነት ይሰጠዋል ማለት ነው። እንዲሁም ከአባቱ ሀብት እጥፉን የመውረስ መብት አለው ማለት ነው።*<br>• ኤሳው ማሰቡን አላቋረጠም። እጅግ በጣም ርቦታል። ወንድሙ እንዲያታልለው እድል ሰጠው። ስለዚህም ብኩርናውን በያዕቆብ ምግብ ለወጠው። (**ዘፍጥረት** 25: 29-34) *የሁለቱንም ልጆች ስራ ተወያዩባቸው። ያዕቆብ ወንደሙን ለብኩርና ሲል ማታለል ነበረበት? ኤሳውስ አንድ ሳንን በማይሞላ ምግብ መሸጥ ይገባው ነበር?*<br>• *በያዕቆብና በኤሳው ምክንያት እግዚአብሔር ደስተኛ ነበር ትላላችሁ?*<br>• *አንዳንዴ እንደኤሳውና እንደያዕቆብ እኛ ሰለምንፈልገው ነገር ብቻ እናስባለን። በራስ ወዳድነት ስንንቀሳቀስ ኃጢአት እንሰራለን።*<br><br>**የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን አጠናቁ።** |
| የመማር ጊዜ | ቁልፍ ጥቅሱን እንደአስፈላጊነቱ አስተምሩ፣ አብራሩ። - **ዘፍጥረት 25: 28 ወይንም ፊልጵስዩስ 2: 3** |
| የክለሳ ጊዜ | • በታሪኩ ውስጥ የተጠቀሱት ሁለቱ ልጆች ስም ማን ይባላል?<br>• ታላቁ ማን ይባላል?<br>• ሁለቱ ልጆች የሚለያዩባቸውን ነገሮች ጥቀሱ።<br>• ብኩርና ምን ማለት ነው?<br>• ያዕቆብ ብኩርናውን ለራሱ የፈለገበት ምክንያት ምንድነው?<br>• ያዕቆብ ኤሳውን ያታለለው እንዴት ነበር?<br>• ከዚህ ታሪክ የምንማራቸው ትምህርቶች ምንድናቸው? |

## <u>ሀ9 ታሪክ 2</u>

**ያዕቆብ አባቱን አታለለ። – ይህ  ታሪክ ያዕቆብ እንዴት እንዳጭበረበረ ይናገራል።**

<table>
<tr><td></td><td>በዚህ ክፍል የምንማራቸው  የሚከተሉትን ነው።<ul><li>ርብቃና ያዕቆብ ይስሐቅን ለማታለል መፈጋቸውን እንማራለን።</li><li>ማጭበርበርና ውሸት መናገር በእግዚአብሔር አይን ትክክል እንዳልሆኑ እንማራለን።</li></ul>ቁልፍ ጥቅስ              ዘፍጥረት 27: 20 ወይንም መዝሙር 32: 2<br>የጥናት ክፍል :          ዘፍጥረት 27: 1-29</td></tr>
<tr><td>መግቢያ</td><td><ul><li>መዋሸት ምን ማለት ነው?</li><li>በዚህ ታሪክ ያዕቆብ አባቱን ዋሸ። ይህ ውሸቱም አባቱንን ወንድሙን እጅግ በጣም ጎዳቸው።</li><li>ሌሎች እንዲህ አይነት ታሪኮችን ታውቃላችሁን? ማለትም ሰዎች ውሸትን ተናግረው ሌሎች ሰዎችን ሲጎዱ አይታችሁ ታውቃላችሁ?</li></ul></td></tr>
<tr><td>የማስተማር ጊዜ</td><td><ul><li>አሁን ይስሐቅ አርጅቷል አይኖቹም ፈዘዋል፣ ማየት አይችሉም። ከመሞቱ በፊት የበኩር ልጁን ኤሳውን መባረክ ፈለገ። ኤሳው የሚወደውን ጣፋጭ ምግብ እንዲያዘጋጅለት ጠየቀው። (ዘፍጥረት 27: 1 – 4) በብሉይ ኪዳን ዘመን አባት ከመሞቱ በፊት የበኩር ልጁን ይባርክ እንደነበር አስረዷቸው።</li><li>ርብቃ ይስሐቅ ልጁን ኤሳውን ሊባርከው እንደሚፈልግ ተደብቃ ሰማች። ከልጇ ከያዕቆብ ጋር ሆነው እንዴት ይስሐቅን አታለው በኤሳው ምትክ ያዕቆብን እንዲባርከው ማድረግ እንደሚችሉ አሴሩ።  እናም ርብቃ ምግብ አበሰለች። የያዕቆብን እጆች በፍየል ፀጉር ሸፈነቻቸው። ይህም ልክ የኤሳው ገላ እንዲመስል ለማድረግ ነበር። (ዘፍጥረት 27: 5 – 17) እያንዳንዱ ወላጅ የሚወደው ልጅ እንደነበረው ለምታስተምሯቸው ልጆች ንገሯቸው።  ርብቃ የምትወደው ልጇ ያዕቆብ ሲሆን ይስሐቅ የሚወደው ልጁ ደግሞ ኤሳው ነበር።  ሁለቱም የሚወዱት ልጃቸው ይህን የብኩርና በረከት እንዲወስድ ይፈልጉ ነበር። አግባብነት የሌለው በቤት ወይንም በት/ቤት የሚከሰት የመድልዎ ምሳሌ ለተማሪዎቻችሁ ጥቀሱላቸው።</li><li>ያዕቆብ የተዘጋጀውን ልዩ ምግብ አቀረበ።  በይስሐቅ ፊት ኤሳው ነኝ ብሎ አታለለው። ይስሐቅም ኤሳው በዚህ ፍጥነት እንዲህ ጣፋጭ ምግብ አዘጋጅቶ መምጣቱ አስገረመው።   (ዘፍጥረት 27: 18 – 20). ያዕቆብና ርብቃ ባደረጉት ነገር እግዚአብሔር የተደሰተ ይመስላችኋል? ከተደሰተ ለምን? ካልተደሰተስ ለምን?</li><li>ይስሐቅ ተጠራጥሯል። እውን ይህ ኤሳው ነውን? እርግጠኛ ለመሆን ፈልጎም በእጁ ላይ ያለውን ፀጉር እንዲዳስሰው ጠየቀው። አዎን! ... እጁ እንደኤሳው እጅ ነው። ድምፁ ግን የያዕቆብን ድምፅ ይመስላል። ይስሐቅ ግራ ተጋባ። ያዕቆብ እንደገና ዋሸ። ለአባቱም እኔ ኤሳው ነኝ አለው።  (ዘፍጥረት 27: 21 – 24)</li><li>ይስሐቅ ያዕቆብ ያቀረበለትን ምግብ በላ። በልቶ ሲጨርስም ያዕቆብ ኤሳው ስለ መሰለው ባረከው። (ዘፍጥረት 27: 25 – 29) ይስሐቅ እንደተታለለ ሲያውቅ ምን የሚሰማው ይመስላችኋል?</li><li>እግዚአብሔር እንዳንዋሽ የሚፈልገው ለምንድነው?</li><li>የጌታ የኢየሱስ ክርስቶስን ምሳሌ አስቡ።</li></ul>የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን አጠናቁ።</td></tr>
<tr><td>የመማር ጊዜ</td><td>ቁልፍ ጥቅሱን እንደአስፈላጊነቱ አስተምሩ፣ አብራሩ። - ዘፍጥረት 27: 20 ወይንም መዝሙር 32: 2</td></tr>
<tr><td>የክለሳ ጊዜ</td><td><ul><li>ይስሐቅ የሚወደው ልጁ ማን ነበር?</li><li>ርብቃ የምትወደው ልጇ ማን ነበር?</li><li>ይስሐቅ ከመሞቱ በፊት ለኤሳው ምን ሊያደርግለት ፈለገ?</li><li>ርብቃ የብኩርናው በረከት ለኤሳው እንዲሆን ትፈልግ ነበር? ለምን?</li><li>ያዕቆብና ርብቃ ይስሐቅን ያታለሉት እንዴት ነበር?</li><li>ይስሐቅ ያዕቆብን ለይቶ ሊያውቀው ያልቻለው ለምን ነበር?</li><li>በዚህ ታሪክ ያዕቆብና ርብቃ እግዚአብሔርን ያስደሰቱ ይመስላችኋል? ለምን?</li></ul></td></tr>
</table>

## ሀ9 ታሪክ 3

## ያዕቆብ እግዚአብሔርን ተገናኘ። – ይህ ታሪክ ስለ እግዚአብሔር ጥበቃ ይናገራል።

**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**

- እግዚአብሔር የተስፋ ቃሎቹን የሚፈፅም አምላክ ስለሆነ በእግዚአብሔር መታመን እንደምንችል እንማራለን።
- እግዚአብሔር ለእኛ ይጠነቀቅልናል።

**ቁልፍ ጥቅስ** **ዘፍጥረት 28: 16 ወይንም መዝሙር 86: 11**

**የጥናት ክፍል :** **ዘፍጥረት 28: 1-22**

### *መግቢያ*

- *ባለፈው ታሪክ ያዕቆብ እንዴት ኤሳውን እንዳታለለው የሚገልፀውን ክፍል ለተማሪዎቻችሁ መልሳችሁ አስታውሷቸው። ኤሳው እጅግ በጣም ስለ ተበሳጨ ሊገድለው አሰበ። ያዕቆብም ለጊዜው መሸሽን መረጠ።*
- *ተማሪዎቻችሁ ልክ እንደያዕቆብ ሆነው እንዲያስቡ ጠይቋቸው። በዚህ መልኩ ከቤት እንዲርቁ ቢደረጉ ምን ይሰማቸዋል?*
- *ምንም እንኳን ያዕቆብ ክፉ ቢያደርግም እግዚአብሔር አሁንም እየጠበቀው እንደሆነ ለተማሪዎቻችሁ ንገሯቸው። የዛሬው ታሪክ እግዚአብሔር ለያዕቆብ ራሱን እንዴት እንደገለጠለት ይነግረናል።*

### የማስተማር ጊዜ

- ይስሐቅ ያዕቆብን ከባረከው በኋላ በካራን ምድር ወደ ሚገኘው ወደ አጎቱ ላባ እንዲሄድ ነገረው። ከዚያም ምድር ሚስት ፈልጎ እንዲያገባ ነገረው። (28: 1–5)
- ያዕቆብ በጉዞው ሌሊት በአንድ ቦታ አረፈ። ለትራስም ድንጋይን ተጠቀመ። *ይህ ምን ሊመስል እንደሚችል ገምቱ!* ተኝቶ ሳለም በሕልሙ ከመሬት ወደ ሰማይ የሚደርስ መሰላል ተመለከተ። የእግዚአብሔር መላእክትም በመሰላሉ ላይ ይወጡና ይወርዱ ነበር። (28: 10–12)
- በመሰላሉ የላይኛው ጫፍም እግዚአብሔር ቆሞበት ነበር። ለያዕቆብም እንደሚባርከውና ዘሩን እንደሚያበዛለት ነገረው። ከእርሱ ጋር እንደሚሆንና አንድ ቀን መልሶ ወደ ተወለደበት ምድር እንደሚያመጣው ቃል ገባለት። (28: 13 – 15) *የተስፋ ቃል ምን ማለት እንደሆነ አስረዷቸው። እኛስ የገባነውን ቃል ሁልጊዜ እንፈፅማለን? ለምን? እግዚአብሔር ሁልጊዜም የተስፋ ቃሉን እንደሚፈፅም ለተማሪዎቻችሁ ንገሯቸው። አይዋሽም ደግሞም ሁሉን ይችላል።*
- ያዕቆብ ከእንቅልፉ ሲነቃ እግዚአብሔር በዚያ ባረፈበት ስፍራ እንዳለ ተረዳ። *የእግዚአብሔርን በዚያ ስፍራ መኖር ሲያስብ ያዕቆብ እንዴት እንደፈራ ለተማሪዎቻችሁ አስረዷቸው። ያዕቆብ እግዚአብሔርን የሚያሳዝኑ ብዙ ነገሮችን አድርጓል። ነገር ግን እግዚአብሔር አሁንም እየተጠነቀቀለትና እየጠበቀው ነው።* ለትራስ የተጠቀመበትን ድንጋይ ወሰደ። በላዩም ዘይት አፈሰሰበት። ያን ቦታም ቤቴል ብሎ ጠራው። እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ቢሆንና ወደ ተወለደበት ምድር ቢመልሰው እግዚአብሔር አምላኩ እንደሚሆን ተሳለ። (28: 16–22) ያዕቆብ እግዚአብሔር ሁልጊዜም ለሰዎች የገባውን ቃል እንደሚፈፅም መማር ነበረበት!
- *እኛም ልክ እንደያዕቆብ ነን። ምክንያቱም ብዙ ስህተቶችን ፈፅመናል። ልክ እንደያዕቆብ እግዚአብሔር እኛንም ይወደናል፤ ይጠነቀቅልንማል። ልጁን ኢየሱስን በእኛ ፈንታ በመስቀል ላይ እንዲሞት እንደላከው አስረዷቸው። ልክ እንደመሰላሉ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እኛን ከእግዚአብሔር ጋር ያገናኘናል።*

**የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን አጠናቁ።**

### የመማር ጊዜ

ቁልፍ ጥቅሱን እንደአስፈላጊነቱ አስተምሩ፣ አብራሩ። - **ዘፍጥረት 28: 16 ወይምመዝሙር 86: 11**

### የክለሳ ጊዜ

- ያዕቆብ ከተወለደበት ምድር የሸሸበት ምክንያት ምን ነበር?
- ያዕቆብ እንደትራስ የተጠቀመው ምን ነበር?
- ያዕቆብ በሕልሙ ያየው ምን ነበር?
- እግዚአብሔር ለያዕቆብ በሕልም የተናገረው ምን ነበር?
- ያዕቆብ ምንም እንኳን ብዙ ስህተቶችን ቢፈፅም እግዚአብሔር ተጠነቀቀለት?
- እግዚአብሔር ስለ እኛ እንደሚጠነቀቅ የምናውቀው እንዴት ነው?
- ያዕቆብ የተንተራሰበትን ድንጋይ ምን አደረገው?
- ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከመሰላሉ ጋር የሚመሳሰለው እንዴት ነው?

## <u>ሀ9 ታሪክ 4</u>

**ያዕቆብ ሚስት አገኘ። – ይህ ታሪክ ያዕቆብ አጎቱ ላባ ምን እንዳደረገው የሚያሳይ ታሪክ ነው።**

| | |
|---|---|
| | **በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>• አታላዩ ያዕቆብ ራሱ እንደተታለለ እንማራለን።<br>• ሌሎች እንዲያደርጉልን የምንሻውን ነገር እኛም ልናደርግላቸው እንደሚገባን እንማራለን።<br>**ቁልፍ ጥቅስ** **ዘፍጥረት 29: 28 ወይም ገላትያ 6: 7**<br>**የጥናት ክፍል :** **ዘፍጥረት 29: 1-30** |
| *መግቢያ* | • ከዚህ በፊት አይታችኋቸው ከማታውቁ የስጋ ዘመዶቻችሁ ጋር ለመኖር ሄዳችሁ ታውቃላችሁ? ምን ስሜት ተሰማችሁ? ወይንም ከልምዳችሁ ተመሳሳይ አጋጣሚ ገጥሟችሁ ከሆነ ተናገሩ። ያዕቆብ በካራን ምድር ከሚገኘው ከአጎቱ ከላባ ጋር ሊኖር እንደሆነ ለተማሪዎቻችሁ አስታውሷቸው።<br>• በዚህ ታሪክ ውስጥ ያሉትን ገፀ ባሕርያት አስተዋውቋቸው። (ላባ ልጆቹ ሊያና ራሔል)<br>• በዚህ ታሪክ ያዕቆብ አንድ ሰው ሲታለል ምን እንደሚሰማው ይማራል። |
| የማስተማር ጊዜ | • ያዕቆብ ወደ ካራን በመጓዝ ላይ ነበር። በጉዞው መጨረሻ ላይ በውኃ ጉድጓድ አጠገብ እረኞችን አገኘ። እነኝህ እረኞችም አጎቱን ላባን ያውቁታል። (**ዘፍጥረት 29: 1 – 8**)<br>• የላባ ልጅ ራሔል በጎቿን እየነዳች ወደዚህ የውኃ ጉድጓድ መጣች። ያዕቆብም በጉድጓዱ አፍ ላይ ያለውን ድንጋይ በማንከባለል ለበጎቿ ውኃ መቅዳትና ማጠጣት እንድትችል ረዳት። (**ዘፍጥረት 29: 9 – 10**)<br>• ያዕቆብ ማን እንደሆነ ለራሔል ነገራት። ራሔልም ወደ ቤት እየሮጠች ሄደች። ለአባቷም ስለ ያዕቆብ ነገረችው። ላባም ያዕቆብ ከእርሱ ጋር እንዲኖር ጠየቀው። (**ዘፍጥረት 29: 11 – 14**) *ያእቆብና ላባ በንግግራቸው ወቅት ያነሷቸውን አንዳንድ ሀሳቦች ለመገመት ሞክሩ።*<br>• ያዕቆብ ላባን ማገልገል ጀመረ። በዚህ መሠረትም ራሔልን ማግባት እንዲችል ሰባት አመት የላባ አገልጋይ ለመሆን ተስማማ። ይሆናል። ያዕቆብ በዚህ የተስማማው ራሔልን እጅግ በጣም ያፈቅራት ስለ ነበረ ነው። (**ዘፍጥረት 29: 15 – 20**)<br>• ነገር ግን ያዕቆብ በላባ ተታለለ። በስምምነታቸው መሠረት ላባ ለያዕቆብ ራሔልን ሚስቱ ትሆነው ዘንድ መስጠት ሲገባው በምትኳ የሰጠው ግን ሊያን ነበር። (**ዘፍጥረት 29: 21 – 27**) *ያዕቆብ መታለሉን ሲያውቅ ምን ይሰማዋል ትላላችሁ? ተማሪዎቻችሁን ያዕቆብ ሌሎችን እንዴት ሲያታልል እንደነበረ አስታውሰው እንዲነግሯችሁ ጠይቋቸው።*<br>• ያዕቆብ ራሔልንም ጨምሮ አገባት። ሆኖም ለተጨማሪ ሰባት አመት ላባን ለማገልገል በመስማማት ነው። (**ዘፍጥረት 29: 29 – 30**) ላባ ከያዕቆብ ይልቅ በብልጠት የተሻለ ይመስላል።<br>• *ያዕቆብ አሁን በገጠመው መጭበርበር ምክንያት ቀድሞ እርሱ የፈፀማቸውን ማጭበርበሮች አስቦ የተፀፀተ ይመስላችኋል?*<br>• *አንዳንዶች ያዕቆብ የሚገባውን አገኘ ብለው ሊናገሩ ይችላሉ። ተማሪዎቻችሁ ስለዚህ ጉዳይ ምን እንደሚያስቡ ጠይቋቸው።*<br><br>**የዘመኑ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን አጠናቁ።** |
| *የመማር ጊዜ* | ቁልፍ ጥቅሱን እንደአስፈላጊነቱ አስተምሩ፣ አብራሩ። - Either **ዘፍጥረት 29: 28 ወይም ገላትያ 6: 7** |
| የክለሳ ጊዜ | • ላባ የሚኖረው የት ነበር?<br>• የላባ ሁለት ሴት ልጆቹ ስም ማን ነበር?<br>• ያዕቆብ ካራን እንደደረሰ ራሔልን የረዳት እንዴት ነበር?<br>• ያዕቆብ የወደዳት የላባ ልጅ ማን ነበረች?<br>• ያዕቆብ ራሔልን ለማግባት ሲል ስንት አመት ለመስራት ነው የተስማማው?<br>• ላባ ያዕቆብን ያታለለው እንዴት ነበር? |

## <u>ሀ10 ታሪክ 1</u>

## እስጢፋኖስ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ መስዋዕት ሆነ። – ይህ ታሪክ እስጢፋኖስ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በጣም ያፈቅር እንደነበር የሚያስረዳ ታሪክ ነው።

<table>
<tr><td></td><td>በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።<ul><li>እስጢፋኖስ እግዚአብሔርንም ጠላቶቹንም ይወድ እንደነበር እንማራለን።</li><li>እስጢፋኖስ በድንጋይ በሚወገርበት ጊዜ ጌታ ኢየሱስ ከአጠገቡ እንደነበርና በሰማይም ሊገናኘው ይጠብቀው እንደነበር እንማራለን።</li></ul>ቁልፍ ጥቅስ 1 ዮሐንስ 4: 19<br>የጥናት ክፍል : የሐዋርያት ሥራ 6: 8-15, 7: 54-60</td></tr>
<tr><td>መግቢያ</td><td><ul><li>ተማሪዎቻችሁ ሌሎች ሰዎችን የረዱባቸውን ጊዜያት እንዲነግሯችሁ ጠይቋቸው።</li><li>ሰዎችን ለመርዳት ፈልጋችሁ እነርሱ ግን እርዳታችሁን እንደማይፈልጉ ቢገልፁላችሁ ምን ይሰማችኋል? እንደውም ቢነቅፏችሁና ሊጎዳችሁ ቢሞክሩስ?</li><li>የዛሬው ታሪክ ሌሎች ሰዎችን ስለ ረዳ ሰው ይነግረናል። ሌሎች ለዚህ መልካም ተግባሩ ምን እንዳደረጉበት እናያለን።</li></ul></td></tr>
<tr><td>የማስተማር ጊዜ</td><td><ul><li>እስጢፋኖስ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ያፈቅር ነበር። ሰዎችን የሚጠቅሙ ተአምራትን ያደርግ ነበር። አንዳንድ አይሁዳውያን ግን እርሱንም ሆነ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን አይወዷቸውም ነበር። በምስጢር ተሰብስበው እስጢፋኖስን ለመጉዳትና ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰዎች ሁሉ ሲል መሞቱን እንዳይናገር ለማድረግ ወሰኑ። (የሐዋርያት ሥራ 6: 8-11)</li><li>እነኝህ ሰዎች በእስጢፋኖስ ላይ የሐሰት ወሬ በመንዛትና ሕዝቡን አነሳሱ። እንዲሁም ወደ ፍርድ ሸንጎ እንዲመጣ በማድረግ ውሳኔ አስወሰኑበት። ለዚህም የሐሰት ምስክሮችን ቆጠሩበት። እነኝህ የሐሰት ምስክሮች እስጢፋኖስ ያላለውን አለ ብለው መሰከሩበት። (የሐዋርያት ሥራ 6: 12-15) እናንተ እስጢፋኖስን ብትሆኑ ኖሮ ምን ይሰማችሁ ይሆን?</li><li>ምንም እንኳን ስለእስጢፋኖስና ስለ ኢየሱስ እየተባለ ያለው ሁሉ ሐሰት ቢሆንም እስጢፋኖስ አልተቆጣም። ኢየሱስ ከእርሱ ጋር እንደሆነ ሰዎች ሁሉ ማስተዋል ችለዋል። በእርግጥም ፊቱ የመልአክ መልክ እስኪመስል ድረስ ተለውጧል። (የሐዋርያት ሥራ 6: 15) እስጢፋኖስ ስለ ኢየሱስ ተሟገተ። ይህ ደግሞ የሰዎቹን ብስጭትና ቁጣ አባሰው። (የሐዋርያት ሥራ 7: 54) በእስጢፋኖስ ላይ ምንም ፍርሃት አልታየበትም። ይልቁንስ ቀና ብሎ ሲመለከት ኢየሱስ የእስጢፋኖስን ወደ ሰማይ መምጣትና ከእርሱ ጋር መሆንን ሲጠብቅ አየው። (የሐዋርያት ሥራ 7: 55-56) እስጢፋኖስ ኢየሱስን ሲያየው ምን የተሰማው ይመስላችኋል?</li><li>ሰዎቹ በዚህን ጊዜ እጅግ በጣም ስለ ተቆጡ ራሳቸውን መቆጣጠር ተሳናቸው። ማንንም መስማት የማይችሉበት ደረጃ ላይ ደረሱ። እስጢፋኖስን ከከተማይቱ ውጪ ወሰዱት። በዚያም በትልልቅ ድንጋዮች ወግረው ገደሉት። ታዲያ ይህን በሚያደርጉበት ጊዜ እስጢፋኖስ ጌታ ኢየሱስ ነፍሱን እንዲቀበልና በድንጋይ የሚወግሩትን ሰዎች ይቅር እንዲላቸው ፀለየ። ከዚያም ሞተ። (የሐዋርያት ሥራ 7: 57-60)</li><li>እስጢፋኖስ ከመሞቱ በፊት ለጠላቶቹ አንድ ነገር እንዲያደርግላቸው ጠየቀ። ይህን ለምን ያደረገ ይመስላችኋል?</li><li>ለፈፀምናቸው መጥፎ ነገሮች ይቅርታን ማግኘት የምንችለው እንዴት ነው?</li></ul>የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን አጠናቁ።</td></tr>
<tr><td>የመማር ጊዜ</td><td>ቁልፍ ጥቅሱን እንደአስፈላጊነቱ አስተምሩ፣ አብራሩ። - 1 John 4: 19. እስጢፋኖስ ለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ያለው ፍቅር የታየው ስለ እርሱ ለመሞት ፈቃደኛ በመሆኑ ነበር። ጌታ ኢየሱስ ለእስጢፋኖስ ያለውን ፍቅር የገለጠው በመስቀል ላይ በመሞት ነበር።</td></tr>
<tr><td>የክለሳ ጊዜ</td><td><ul><li>እስጢፋኖስ በቤተ ክርስቲያን ሰዎችን ይረዳ ነበር። እንዴት ነበር ሰዎችን የሚረዳው?</li><li>ሁሉም ሰው እስጢፋኖስን ይወደው ነበርን? ለምን?</li><li>አይሁዳውያውኑ እንዴት ሰዎችን በእስጢፋኖስ ላይ ያነሳሱት ነበር?</li><li>በኢየሱስና በእስጢፋኖስ ላይ በሐሰት ሲመሰከር እስጢፋኖስ ምላሹ እንዴት ነበር?</li><li>እስጢፋኖስ ወደ ሰማይ ሲመለከት ምን አየ?</li><li>ሰዎቹ በእስጢፋኖስ ላይ ምን አደረጉ?</li><li>እስጢፋኖስ ምን ብሎ ፀለየ?</li><li>እኛስ እንዴት የኃጢአት ይቅርታን ማግኘት የምንችለው?</li></ul></td></tr>
</table>

## <u>ሀ10 ታሪክ 2</u>

## ፊሊጶስ መልካሙን ዜና ሰበከ። – ይህ ታሪክ አንድ አፍሪካዊ በኢየሱስ ስለ ማመኑ የሚናገር ታሪክ ነው።

**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**

- ኃጢአታችን ይቅር እንዲባል በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን እንዳለብን እንማራለን።
- እግዚአብሔር የመጽሐፍ ቅዱስ አስቸጋሪ ክፍሎችን እንኳን ሳይቀር እንድናስተውል እንደሚረዳን እንማራለን።

**ቁልፍ ጥቅስ** **የሐዋርያት ሥራ 8: 35**

**የጥናት ክፍል :** **የሐዋርያት ሥራ 8: 26-40**

### *መግቢያ*

- *ምድረ በዳ ምን እንደሚመስል ያውቁ እንደሆነ ተማሪዎቻችሁን ጠይቋቸው። ወደ ምድረ በዳ ሄዳችሁ ለማታውቁት ሰው ስለ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ አዳኝነት እንደትናገሩ ብትታዘዙ ትሄዳላችሁ?*
- *ወይም ለመረዳት ከባድ የሆነ ነገር ገጥሟችሁ ያውቃል? ለምሳሌ መጽሐፍ፣ የሒሳብ ጥያቄ ወዘተ... ማን ረዳችሁ?*

### የማስተማር ጊዜ

- ፊሊጶስ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ አምኗል። እንዲሁም በየከተማው እየተዘዋወረ ይህንኑ ይሰብክ ነበር። አንድ ቀን መልአክ ተገናኘውና በምድረ በዳ መካከል በሚያልፍ ወደ አንድ መንገድ እንዲሄድ ያዘዋል። *(ስለዚህ ፊሊጶስ ምን ሊያስብ ይችላል?)* ፊሊጶስ ሰረገላ ወደ እረሱ ሲቀርብ እንዴት እንዳየ አስረዷቸው። በዚህ ሰረገላ ውስጥ ያለው ሰው ወደ አገሩ በመመለስ ላይ የነበረ አንድ ኢትዮጵያዊ ባለስልጣን ሆኖ ተገኘ። (ይህን አብራሩ።) (**የሐዋርያት ሥራ 8: 26-28**) *ይህ ኢትዮጵያዊ ስለ ማን ነበር መስማት የፈለገው?*
- ከዚያም መንፈስ ቅዱስ ፊሊጶስን ወደዚህ ሰው እንዲሄድና እንዲገናኘው አዘዘው። ይህ ሰው ከትንቢተ ኢሳያስ ጮክ ብሎ ያነብ ነበር። ፊሊጶስም የሚያነበውን ነገር ተረድቶት እንደሆነ ጠየቀው። ሰውየው ግን ግራ መጋባቱን ነገረው! (**የሐዋርያት ሥራ 8: 29-31**). *ከሚያነባቸው ጥቅሶች መካከል አንደኛው የሚናገረው አንድ ሰው እንደጠቦት ለእርድ ሲነዳ የሚገልፀውን ነበር። (ጠቦት ለመታረድ ምንም ተቃውሞ እንደማያሳይ አስረዷቸው።)* ፊሊጶስም ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የሚናገረው ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ ኃጢአታችን በመስቀል ላይ እንደሞተ መሆኑን ለዚህ ኢትዮጵያዊ ባለስልጣን ገለፀለት። *(ኢየሱስ ስለ ኃጢአታችን ለመሞት መፍቀዱን አስረዷቸው።)*
- ያኔ ኢትዮጵያዊው ኃጢአተኛ እንደሆነና የእግዚአብሔር ይቅርታ እንደሚያስፈልገው ተረዳ። ያለማመንታት ኢየሱስ በእርሱ ፈንታ መሞቱን አመነ። (**የሐዋርያት ሥራ 8: 32-35**)
- ፊሊጶስ አጠመቀመው። በዚህም የኢየሱስ ክርስቶስ ተከታይ መሆኑን አረጋገጠ። *(ጥምቀትን አብራሩላቸው።) በዚህ ሰው ሕይወት ውስጥ የተያውን ለውጥና ደስታ አሳዩቸው።*
- መንፈስ ቅዱስ ፊሊጶስ ለሌሎችም ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ይነግራቸው ዘንድ ወደ ሌላ ቦታ ወሰደው።(**የሐዋርያት ሥራ 8: 36-40**)

*እግዚአብሔር ሁሉም ሰዎች ኢየሱስ በኃጢአታቸው ምክንያት እንደሞተላቸው እንዲያውቁ ይፈልጋል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉ እውነቶችን እንድናስተውል ስለ ሚረዱን ሰዎች አውሩ። ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ መልካሙን ዜና ስለ ሰማን እግዚአብሔርን ማመስገን አለብን።*

**የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን አጠናቁ።**

### የመማር ጊዜ

ቁልፍ ጥቅሱን እንደአስፈላጊነቱ አስተምሩ፣ አብራሩ። - **የሐዋርያት ሥራ 8: 35**

### የክለሳ ጊዜ

- መልአኩ ፊሊጶስን ወዴት እንዲሄድ ነው የነገረው?
- ሰውየው የምን አገር ሰው ነበር?
- ፊሊጶስ ወደዚህ ሰው ለምን የሄደው ነበር?
- ይህ ሰው ሲያነብ የነበረው ስለ ምን ነበር የሚናገረው?
- ፊሊጶስ የሚያነበውን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ መሆኑን ካስረዳው በኋላ ሰውየውም ምን አደረገ?
- የተጠመቀው የት ነበር?
- ወደ አገሩ ሲጓዝ የተሰማው ስሜት ምን ነበር?
- የኃጢአት ይቅርታ የምናገኘው እንዴት ነው?

**<u>ሀ10 ታሪክ 3</u>**

**ሳውልና አንፀባራቂው ብርሃን! – ይህ  ታሪክ የሰዎችን ሕይወት መለወጥ ስለ ሚችለው የእግዚአብሔር ኃይል ይተርካል።**

| | |
|---|---|
| | **በዚህ ክፍል የምንማራቸው  የሚከተሉትን ነው።**<br>• ኢየሱስ ምንም እንኳን ሰዎች ቢጠሉትም እንኳን ሰዎችን ሁሉ እንደሚያፈቅርና ለሰዎች ሁሉ እንደሞተ  እንማራለን።<br>• ጌታ ኢየሱስ ብቻ ሕይወታችንን መለወጥ ስልጣን እንዳለው እንማራለን።<br>**ቁልፍ ጥቅስ** **2 ቆሮንቶስ 5: 17**<br>**የጥናት ክፍል :** **የሐዋርያት *ሥራ* 9: 1-9** |
| *መግቢያ* | • ሳውል ኢየሱስን የሚጠላ አይሁዳዊ ነበር። ኢየሱስን የሚከተሉትን ሰዎች በሙሉ እጅግ በጣም ሰለሚጠላቸው ሁሉንም *መግደልና ሲገደሉ ማየትን በጣም ይመኝ ነበር። እስጢፋኖስ ተወግሮ ሲሞት በዚያ እንደነበረና ምን እንዳደረገ አስረዷቸው።* (ታሪክ 1)<br>• *ተማሪዎቻችሁ ሳውልን ለጓደኝነት እንደሚመርጡ  ጠይቋቸው። ከመረጡት ለምን? ካልመረጡትስ ለምን?* |
| የማስተማር ጊዜ | • አንድ ቀን ሳውል ክርስቲያኖችን አስሮ በወህኒ ቤት ለማኖር ወደ ደማስቆስ በመጓዝ ላይ ነበር። (**የሐዋርያት *ሥራ* 9: 1-2**) *በዚህ ጉዞ ላይ እንዳለ የሳውል አመለካከትና ስሜት ምን እንደሚመስል ተወያዩበት።*<br>• ወደ ደማስቆስ በመቃረብ ላይ ሳለ በድንገት ኃይለኛ አንፀባራቂ ብርሃን አየ። በዚህ ጊዜ መሬት ላይ ወደቀ። *ሳውል የሰማቸውን ቃላትና የሳውልንም ምላሽ  እንዳሉ ተጠቀሙባቸው። አሁን ደግሞ የሳውል ስሜት ምን እንደሚመሰል ግለፁላቸው።*  (**የሐዋርያት *ሥራ* 9: 3-4**)<br>• የሰማው ድምፅ እርሱ ኢየሱስ እንደሆነ ተናገረ። *ሳውል አሁን ምን እንደገባው ግለፁላቸው። ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነና ሕያው እንደሆነ እንዲሁም እስከዛሬ ድረስ ስለ ኢየሱስ የነበረው አስተሳሰብ በሙሉ ትክክል አለመሆኑን ተገነዘበ።* ኢየሱስ ወደ ደማስቆስ ከተማ እንዲሄድና በዚያ ሲደርስ ምን ማድረግ እንደሚገባው የሚነግሩት ሰዎችን እንደሚገናኝ ነገረው። ከሳውል ጋር የነበሩ ሰዎች እጅግ ተገረሙ። ምክንያቱም ከሳውል ጋር የሚነጋገረውን ድምፅ ይሰሙ ነበር። ነገር ግን ያዩት ምንም ነገር አልነበረም። (**የሐዋርያት *ሥራ* 9: 5-7**)<br>• ሳውል ሲነሳ ማየት አልቻለም ነበር። ሰዎች እጁን ይዘው በመምራት ወደ ከተማ ይዘውት ሄዱ። ለሶስት ቀን ማየት አልቻለም፤ እህልም ሆነ ውኃ አልቀመሰም።  (**የሐዋርያት *ሥራ* 9:  8-9**) *ማየት ባለመቻሉ ምን የተሰማው ይመስላችኋል?*<br>• *ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ መልኩ ሳውልን መገናኘት ለምን እንደፈለገ ተወያዩበት። ሳውል ኢየሱስንና ተከታዮቹን ይጠላቸው እንደነበረ ተማሪዎቻችሁን አስታውሷቸው።  ሳውል ሁሉም ተገድለው ማየትን ነበር የሚፈልገው። ሆኖም ኢየሱስ ክርስቶስ ሳውልን ስለ ሚወደው አዳነው። የእርሱ ተከታይ መሆን ባይገባውም ተከታዩ አደረገው። ጌታ ኢየሱስ የሳውልን ሕይወት ሙሉ በሙሉ ለመለወጥ ፈለገ።*<br>• *ጌታ ኢየሱስ ኃጢአታችንን እንዲወገድልን ና አዲስ ሕይወት ለመጀመር ጌታ ኢየሱስ ያስፈልገናል።*<br>**የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን አጠናቁ።** |
| የመማር ጊዜ | ቁልፍ ጥቅሱን እንደአስፈላጊነቱ አስተምሩ፣ አብራሩ።  - **2 Corinthians 5: 17**  የእኛ ሕይወት የሚለወጠውና አዲስ የሚሆነው በክርስቶስ ስንስሆን ነው። ይህን ከሳውል ሕይወት መለወጥ ጋር አዛምዱት። |
| የክለሳ ጊዜ | • ሳውል የሚጓዘው ወዴት ነበር?<br>• የሚጓዘው ለምን ነበር?<br>• ያየው ምን ነበር?<br>• የሰማውስ ምን ነበር?<br>• የሰማው ድምፅ ምን አለው?<br>• የሚናገረው ኢየሱስ መሆኑን ሲገነዘብ ጳውሎስ ምን ተረዳ?<br>• ሳውል ለሶስት ቀን ያላደረገው ምን ነበር?<br>• አዲስ ሕይወት ሊሰጠን የሚችለው ብቸኛው ሰው ማን ነው? |

## ሀ10 ታሪክ 4

**ሳውል ተለወጠ። – ይህ ታሪክ እግዚአብሔር ሳውልን ለሌሎች ሰዎች መልካሙን ዜና እንዲናገር እንደተጠቀመበት የሚናገር ታሪክ ነው።**

| | |
|---|---|
| | **በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>• እግዚአብሔር ሊረዳን እንደሚፈልግና ለዚህም ሰዎችን ወደ እኛ እንደሚልክ እንማራለን።<br>• ልክ እንደሳውል ዛሬም እግዚአብሔር የሰዎችን ሕይወት ለውጦ ለእርሱ የሚጠቅሙ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል።<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ** **የሐዋርያት *ሥራ* 9: 20**<br>**የጥናት ክፍል : የሐዋርያት *ሥራ* 9: 10-23** |
| *መግቢያ* | • የሳውልን ሕይወት ታሪክ የመጀመሪያ ክፍል መልሳችሁ እዩት። "አሮጌው" ሳውል ሕይወቱ ምን እንደሚመስል ታስታውሳላችሁ? በደማስቆስ ይኖሩ የነበሩ የክርስቶስ ተከታዮች ስለ "አሮጌው" ሳውል ምን ያስቡ እንደነበረ መገመት ትችላላችሁ? (ፍርሃት...)<br>• ሳውልን እንደእግዚአብሔር ቤተ ሰብ አባል አድርገው መቀበል እንዲችሉ እግዚአብሔር የደማስቆስ ከተማ ነዋሪዎችን ሊያዘጋጃቸው ያስፈልገው ነበር። ምን እንደሆነ እስኪ እንመልከት... |
| *የማስተማር ጊዜ* | • እግዚአብሔር ሐናንያን በሕልም ተናገረው። ሳውልንም ፈልጎ እንዲያገኘው ነገረው። (**የሐዋርያት *ሥራ* 9: 10-12**) *ሐናንያ መሄድ የሚፈልግ ይመስላችኋል? ለምን?*<br>• ሐናንያ ሳውል ሊያስረውና ሊገድለው እንደሚችል ስላሰበ ፈራ። እግዚአብሔርም ምንም ስጋት እንዳይገባው ነገረው። ምክንያቱም ሳውልን ለተለየ ስራ መርጦታልና ነው። ይህም የተለየ ስራ ስለ እግዚአብሔር ምንም ሰምተው ለማያውቁ ሰዎች መልካሙን ዜና መንገር ነው። (**የሐዋርያት *ሥራ* 9: 13-16**)<br>• ሐናንያ ታዞ ሳውል ወዳለበት ቦታ ሔደ። ወንድም ብሎም ጠራው። (ለምን ወንድማማች ሊሆኑ እንደቻሉ ግለፁላቸው።) ጌታ ኢየሱስ እንደላከውም ነገረው። በሳውል አይኖች ላይ እጆቹን ጭኖ ፀለየለት። እንደገናም አየ። ሳውል በመንፈስ ቅደስ ተሞላ። ከተጠመቀ በኋላ ጥቂት ምግብ ቀመሰ። (**የሐዋርያት *ሥራ* 9: 17-19ሀ**) *ሳውል የሐናንያ ጉብኝትን እንዴት የሚያየው ይመስላችኋል?*<br>• ከጥቂት ቀናት በኋላ ሳውል በደማስቆስ የሚኖሩ ሌሎች የክርስቶስ ተከታዮችን ተገናኛቸው። ወዲያውም ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ መስበክ ጀመረ። *በደማስቆስ የሳውልን ስብከት የሰሙ ምን ምላሽ ምን ሊሆን እንደሚችል ግለፁላቸው። ይህ የሚጠብቁት ሳውል አልነበረም!*<br>በደማስቆስ ይኖሩ የነበሩ አይሁዳውያን የሳውልን ሕይወት ለውጥና ይህን ተከትሎ የሰበከውን ስብከት አልወደዱትም። ሊገድሉት ተማከሩ። ስለዚህ ሳውል ከደማስቆስ በግንብ በኩል በቅርጫት አንጠልጥለው እንዲያመልጥ አደረጉት። (**የሐዋርያት *ሥራ* 9: 19-25**) *የሳውል ሕይወት መለወጥና እንደኢየሱስ ክርስቶስ ተከታይ በዙሪያው የከበቡትን ሁኔታዎች አነፃፅሯቸው።*<br>**የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን አጠናቁ።** |
| *የመማር ጊዜ* | ቁልፍ ጥቅሱን እንደአስፈላጊነቱ አስተምሩ፣ አብራሩ። - **የሐዋርያት *ሥራ* 9: 20** |
| *የክለሳ ጊዜ* | • ሓናንያን እግዚብሔር እንዴት የተናገረው ነበር?<br>• ሐናንያ ወደ ሳውል ለመሄድ የፈራው ለምንድን ነበር?<br>• የሳውል አዲሱ ስራው ምን ነበር?<br>• ሐናንያ እጆቹን በሳውል አይኖች ላይ ጭኖ ሲፀልይ ምን ሆነ?<br>• ሐናንያ ሳውልን ሲጎበኘው ሳውል የተቀበለው ሌላኛው ስጦታ ምን ነበር?<br>• ሳውል ወዲያውኑ ያደረገው ምን ነበር?<br>• ሳውል በቅርጫት ውስጥ እንዲያመልጥ ያደረጉት ለምን ነበር?<br>• ልክ እንደሳውል ሕይወታችን ሙሉ በሙሉ የሚለወጠው እንዴት ነው? |

<u>ሀ11 ታሪክ 1</u>

## ጳውሎስ (ሳውል) በአንጾኪያ – ይህ ታሪክ በእግዚአብሔር ስራ ውስጥ ስለ መሳተፍ ይናገራል።

**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው። አንኪያም**

- በጌታ በኢየሱስ የሚያምኑ ሰዎች “ክርስቲያኖች” ተብለው እንደሚጠሩ እንማራለን።
- በእርሱ ስንታመን እግዚአብሔር ለእኛ የተለየ እቅድ እንዳለው እንማራለን። ከእርሱ ጋር አብረን ሰራተኞች እንድንሆን እንደሚፈልግም እንማራለን።

**ቁልፍ ጥቅስ** **የሐዋርያት *ሥራ* 11: 26**
**የጥናት ክፍል :** **የሐዋርያት *ሥራ* 11: 19-26**

### *መግቢያ*

- *ተማሪዎቻችሁ በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ እንዴት እርዳታ መስጠት እንደሚችሉ ጠይቋቸው። መምህራቸውን እንዴት መርዳት ይችላሉ? እናቶቻቸው ቢታመሙ እንዴት መርዳት እንደሚችሉ ጠይቋቸው?*
- በዛሬው ታሪክ ሁለት ሰዎች በእግዚአብሔር ስራ ውስጥ እንዴት በአንድ ላይ እርዳታ እንደለገሱ እናያለን።

### የማስተማር ጊዜ

- የጌታ የኢየሱስ መልካም ዜና በሁሉም ስፍራ እየተሰራጨና ቤተ ክርስቲያንም እያደገች በመሄድ ላይ ነበር። አንዳንድ አማኞች ለኑሮ አንጾኪያ ወደ ምትባል ከተማ ሄዱ። በዚያም ስለ መልካሙ ዜና ምንም ላልሰሙ ሰዎች ይነግሯቸው ነበር። ብዙ ሰዎችም በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ያምኑ ነበር። **(የሐዋርያት *ሥራ* 11: 19-21)**
- በኢየሩሳሌም የነበረችው ቤተ ክርስቲያንም በአንጾኪያ እየሆነ ስለ ነበረው ታላቅ ነገር ሰማች። *አማኞች ምን የተሰማቸው ይመስላችኋል? (ታላቅ ደስታ)* በርናባስ የተባለውን አገልጋይ ወደ አንጾኪያ በመላክ በዚያ እየሆነ ስለ ነበረው ጉዳይ በተጨማሪ ለማወቅ ወሰኑ። በርናባስም ወደ አንጾኪያ ሄደ። በዚያም ብዙ አዳዲስ አማኞችን ስላየ እጅግ ደስ ተሰኘ። አዳዲሶቹ አማኞች ሊማሩ የሚገባቸውን ነገር በሙሉ በርናባስ አስተማራቸው። እንዲሁም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን እንዲወዱ አበረታታቸው። **(የሐዋርያት *ሥራ* 11: 22-24)** *በርናባስ ምን አይነት ሰው ነበር?*
- በርናባስ በአንጾኪያ ሳለ ብዙ ስራዎችን ይሰራ ነበር። ስለዚህም ረዳት አስፈለገው። እግዚአብሔርም ከጥቂት አመታት በፊት ስላገኘው ስለ ሳውል አሳሰበው። ሳውል ጌታ ኢየሱስን ከተገናኘው በኋላ ወደ ተወለደበት ወደ ጠርሴስ ተመልሶ ሄዶ ነበር። በርናባስ ወደ ጠርሴስ ሄዶ ሳውልን ወደ አንጾኪያ ይዞት ተመለሰ። በዚያም በእግዚአብሔር ስራ አብሮት ሠራተኛ እንዲሆንና እንዲያግዘው አደረገ። **(የሐዋርያት *ሥራ* 11: 25-26).**
- *አንጾኪያ ለሳውል/ለጳውሎስ በጣም አስፈላጊ ከተማ እንደነበረች ግለፁላቸው። ምክንያቱም የሚሲዮናዊነት አገልግሎቱን የጀመረው በዚህች ከተማ ስለ ነበረ ነው። ይህም እግዚአብሔር ለእርሱ ያዘጋጀው ልዩ ስራ ነበር።* ሳውልና በርናባስ ቀጣዩን አንድ አመት አብረው አማኞችን በማስተማር በአንጾኪያ ውስጥ አሳለፉ። በዚያን ጊዜ በዚያ የሚገኙ አማኞች ለመጀመሪያ ጊዜ “ክርስቲያኖች” ተብለው ተጠሩ። **(የሐዋርያት *ሥራ* 11: 26)**
- *በኢየሱስ ክርስቶስ ስናምን እኛም “ክርስቲያኖች” እንሆናለን። የኢየሱስን ስም እንጋራለን! ልክ እንደጳውሎስ እግዚአብሔር ለሁሉም ክርስቲያኖች ልዩ እቅድ አለው። ክርስቲያኖች ረዳቶቹ እንዲሆኑ ይፈልጋል።*
- *ክርስቲያን ለመሆን ምን ማድረግ አለብን?*
- *ክርስቲያኖች ከሆንን የእግዚአብሔር ረዳቶች መሆን የምችልባቸው መንገዶች ምንድናቸው?*

**የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን አጠናቁ።**

### *የመማር ጊዜ*

ቁልፍ ጥቅሱን እንደአስፈላጊነቱ አስተምሩ፣ አብራሩ። - **የሐዋርያት *ሥራ* 11: 26**

### የክለሳ ጊዜ

- ቤተ ክርስቲያን በማደግ ላይ የነበረችው በየትኛው ከተማ ነበር?
- በኢየሩሳሌም የነበሩት አማኞች ወደ አንጾኪያ የላኩት ማንን ነበር?
- በርናባስ በአንጾኪያ ምን አደረገ?
- ከጥቂት ቆይታ በኋላ በርናባስ ምን አስፈለገው?
- በርናባስ ማንን ፍለጋ ሄደ?
- በርናባስና ሳውል በአንጾኪያ ምን ያህል ጊዜ አብረው አሳለፉ?
- በኢየሱስ ለሚያምኑ ሰዎች አዲስ የወጣላቸው ስም ምን ነበር?
- ሳውል የሰራው የማንን ስራ ነበር?

**ሀ11 ታሪክ 2**

**ጳውሎስ (ሳውል) በቆጵሮስ – ይህ ታሪክ ስለ ጌታ ኢየሱስ ለሌሎች ስለ መንገር ያወሳል።**

| | |
|---|---|
| | **በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>• በኢየሱስ በማመን ትክክለኛ ምርጫ መምረጥ እንደሚገባን እንማራለን።<br>• እኛም ለሌሎች ሰዎች ስለ ኢየሱስ ልንነግራው እንደሚገባን እንማራለን።<br>**ቁልፍ ጥቅስ** **ማቴዎስ 28: 19**<br>**የጥናት ክፍል : የሐዋርያት ሥራ** 13: 1-12 |
| *መግቢያ* | • *ተማሪዎቻችሁ በቡድን ሆነው እንዲሰሩ አድርጓቸው። ስለ ኢየሱስ ማሰብ የሚችሏቸውን ነገሮች በሙሉ እንዲያስቡ አድርጓቸው።*<br>• የዛሬው ታሪክ ጳውሎስ፣ በርናባስና ዮሐንስ ማርቆስ ለሕዝቡ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ መናገራቸው የሚያወሳ ታሪክ ነው። (ስለ ሳውል ስም መለወጥ ግለፁላቸው።) |
| የማስተማር ጊዜ | • አንድ ቀን በአንጾኪያ የሚኖሩ ክርስቲያኖች በአንድ ላይ ተሰብስበው ነበር። ጳውሎስና በርናባስም በዚያ ነበሩ። መንፈስ ቅዱስ በዚያ ለነበሩ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በግልፅ በርናባስና ጳውሎስ እግዚአብሔር ላዘጋጀላቸው ሌላ ስራ የተለዩ መሆናቸውን ነገራቸው። ከፀሎት በኋላም በርናባስ፣ ጳውሎስና የሐንስ ማርቆስ (ይህ የበርናባስ የወንድሙ ልጅ ነበር) በጀልባ ተሳፍረው ወደ ቆጵሮስ ተጓዙ። (**የሐዋርያት ሥራ** 13: 1-4)<br>• እዚያ እንደደረሱም መልካሙን ዜና እየሰበኩ ዞሩ። ጳፉ በሚባል ቦታም የቆጵሮስ አገረ ገዢን ከሚያገለግል አንድ ጠንቋይ ጋር ተገናኙ። አገረ ገዢው ስለ ጳውሎስና ስለ ነበርናባስ ሰምቶ ስለ ነበር ሊገናኛቸው ይፈለግ ነበር። አገረ ገዢው የእግዚአብሔርን ቃል ሰማ። ሆኖም ጠንቋዩ ኤልማስ እንዳያምን ለመከላከል ሞከረ። (**የሐዋርያት ሥራ** 13: 5-8)<br>• ሳውል ይህ ጠንቋይ የሰይጣንን ስራ እንደሚሰራ ያውቅ ነበር። ሳውል በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ተሞልቶ ነበር። በቀጥታ ወደ ጠንቋዩ አይኖች ተመልክቶም የሚሰራው ስራ የሰይጣንን ስራ እንደሆነና አይኑ እንደሚታወር ነገረው። ልክ ጳውሎስ ተናግሮ እንደጨረሰ ኤልማስ ታወረ። በአጠገቡም የሚመራው ሰው ፍለጋ እጆቹን ዘረጋ። (**የሐዋርያት ሥራ** 13: 9-11) *ጌታ ኢየሱስን መቃውም አደገኛ እንደሆነ ግለፁላቸው።*<br>• አገረ ገዢው የእግዚአብሔርን ኃይል ታላቅነት አየ። በኢየሱስ ክርስቶስም አመነ። (**የሐዋርያት ሥራ** 13: 12)<br>• *ጳውሎስ፣ በርናባስና ዮሐንስ ማርቆስ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመናቸው ትክክለኛ ምርጫ መረጡ። ኤልማስ ግን የተሳሳተ ምርጫ መረጠ። ኢየሱስ እኛም እንድናምነው ይፈልጋል።*<br>• *ለምን ይመስላችኋል ስለ ኢየሱስ የሚነገረው መልካም ዜና ብቻ እጅግ በጣም አስፈላጊ ዜና የሚሆነው?*<br>• *ስለ ጌታ ኢየሱስ ለሰዎች የሚናገርና በሌላ ቦታ የሚኖር ሰው ታውቃላችሁ?*<br>• *ለሌሎች ሰዎች ስለ ኢየሱስ እንዴት መናገር ትችላላችሁ?*<br><br>**የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን አጠናቁ።** |
| የመማር ጊዜ | ቁልፍ ጥቅሱን እንደአስፈላጊነቱ አስተምሩ፣ አብራሩ። - **ማቴዎስ** 28: 19. እነኝህ ቃላት ኢየሱስ ክርስቶስ ከምድር ከማረጉ በፊት የተናገራቸው ቃላት መሆናቸውን ግለፁላቸው። በስፍራ ሁሉ ያሉ ሰዎች መልካሙን ዜና ሰምተው በእርሱ እንዲያምኑና እንዲድኑ የጌታ የኢየሱስ ፈቃዱ ነው። |
| የክለሳ ጊዜ | • ጳውሎስና በርናባስ የእግዚአብሔርን ልዩ ስራ እንዲሰሩ የላካቸው ማን ነበር?<br>• ከእነርሱ ጋር አብሮ የተጓዘው ማን ነበር?<br>• እንዴት ነበር የተጓዙት?<br>• የተጓዙበት የደሴት ስም ምን ይባል ነበር?<br>• በጳፉ ማንን አገኙ?<br>• በጳፉ በኢየሱስ ክርስቶስ ያመነው ሰው ማነው?<br>• በጠንቋዩ ላይ ምን ሆነ?<br>• በዛሬው ቁልፍ ጥቅስ ላይ ተናጋሪው ማነው? |

## <u>ሀ11 ታሪክ 3</u>

**ጳውሎስ ልዲያን ተገናኛት። – ይህ ታሪክ በኢየሱስ ክርስቶስ ስላመነች አንዲት ሴት ይናገራል።**

| | |
|---|---|
| | **በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>• በኢየሱስ ክርስቶስ የሚያምን ሁሉ እንደሚድን እንማራለን።<br>• ለእግዚአብሔር ስለ ማንኛውም ነገርና በማንኛውም ስፍራ ሆነን መናገር እንደምንችል እንማራለን።<br>**ቁልፍ ጥቅስ** **የሐዋርያት *ሥራ* 2: 21**<br>**የጥናት ክፍል : የሐዋርያት *ሥራ* 16: 6-15** |
| *መግቢያ* | • *ተማሪዎቻችሁ ራቅ ወዳለ ስፍራ ተጉዘው ያውቁ እንደሆነ ጠይቋቸው። የት ነበር የተጓዛችሁት? ምን ያህል ጊዜ ፈጀባችሁ? በዚያ ማንን አገኛችሁ?*<br>• *የዛሬው ታሪክ ጳውሎስና ወዳጆቹ ስለ ተጓዙት ጉዞ የሚናገር ታሪክ ነው።* |
| የማስተማር ጊዜ | • ጳውሎስና ሁለቱ የስራ አጋሮቹ ሲላስና ጢሞቴዎስ ከአገር ወደ አገር እጅግ በጣም ረጅም ጉዞ ተጓዙ። መንፈስ ቅዱስም በትክክል የት መሄድ እንዳለባቸው ያሳያቸው ነበር። በሄዱበት ቦታ ሁሉ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ሊሰሙ የሚገባቸው ብዙ ሰዎች ይገጥሟቸው ነበር። (**የሐዋርያት *ሥራ* 16: 6-8**)<br>• በድንገትም በባሕር ዳርቻ ወዳለች አንዲት ከተማ ደረሱ። በዚያን ምሽት ጳውሎስ በአይነቱ ልዩ የሆነ ሕልም አየ። በዚህም ሕልም አንድ ከመቄዶንያ የሆነ ሰው እነጳውሎስ ከእርሱ ጋር እንዲሄዱና እንዲረዳቸው ሲጠይቀው ያያል። ጳውሎስ በግልፅ የት መሄድ እንዳለባቸው እያሳያቸው እንደሆነ አወቀ። (**የሐዋርያት *ሥራ* 16: 9-10**)<br>• *እግዚአብሔር በዚያ የሚኖሩ ሰዎች ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲሰሙ ስለ ፈለገ ጳውሎስንና የስራ አጋሮቹን ወደዚህ ቦታ ላካቸው። መኖሪያችን የትም ቢሆን እግዚአብሔርን የሚያሳስበው ጉዳይ አይደለም። ስለ ልጁ መልካም ዜና መስማት አለብን።*<br>• ወዲያው ወደዚያ የሚያመራ መርከብ አግኝተው ተሳፉሩ። ፊልጵስዩስ ወደ ምትባል ከተማም ደረሱ። በሰንበት ቀንም ጳውሎስና የስራ አጋሮቹ ከከተማው ውጪ ወደ ሚገኘው የወንዝ ዳርቻ ተጓዙ። በዚያም ለፀሎት የመጡ የከተማይቱን አንዳንድ ሴቶች አገኙ። (**የሐዋርያት *ሥራ* 16: 11-13**) *በዚያ በወንዝ ዳርቻ የነበሩ ሴቶች ወደ እግዚአብሔር ይፀልዩ ነበር። ከእግዚአብሔር ጋር መነጋገር የንምችለው በየትኛው ስፍራ ነው? (ከእግዚአብሔር ጋር በየትኛው ስፍራ ሆነን መነጋገር እንችላለን።)*<br>• ከሚፀልዩት ሴቶች መካከል አንደኛዋ ልዲያ ትባላለች። የሐር ጨርቅ በመሸጥ ትተዳደር ነበር። በእግዚአብሔር ለረጅም ጊዜ ያመነች ሴት ነበረች። ነገር ግን ስለ እግዚአብሔር ልጅ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ በፍፁም ሰምታ አታውቅም። ልዲያ ጳውሎስ የተናገረውን በሙሉ በጥንቃቄ አደመጠች። በልቧም ጳውሎስ የተናገረው ነገር በሙሉ ትክክል እንደሆነ ተረዳች። ስለዚህም በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ አመነች። ጳውሎስ እርሷ ወደ ምትኖርበት ከተማ በመምጣቱ ተደሰተች። (**የሐዋርያት *ሥራ* 16: 14-15**) የልዲያ ቤተ ሰቦቿም ጭምር ክርስቲያኖች ሆኑ። ሁሉም ተጠመቁ። ልዲያም ጳውሎስና የስራ አጋሮቹ በቤቷ እንዲኖሩ ጋበዘቻቸው።<br>• *ከእግዚአብሔር ጋር ስለ ምን መነጋገር እንችላለን? (ተማሪዎቻችሁ ከዚህ ጋር የተገናኙ ሀሳቦችን ማቅረብ እንዲችሉ ፍቀዱላቸው። ከዚያም ከእግዚአብሔር ጋር ስለ ማንኛውም ጉዳይ መነጋገር እንደምንችል ግለፁላቸው።)*<br><br>**የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን አጠናቁ።** |
| የመማር ጊዜ | ቁልፍ ጥቅሱን እንደአስፈላጊነቱ አስተምሩ፣ አብራሩ። - **የሐዋርያት *ሥራ* 2: 21.** የጌታ የኢየሱስን ስም መጥራት ማለት ከኃጢአታችን እንዲያድነን መጠየቅ ማለት እንደሆነ ግለፁላቸው። በዚህ ታሪክ ልዲያ ያደረገችው ይህንኑ ነበር። |
| የክለሳ ጊዜ | • ከጳውሎስ የስራ አጋሮች አንዱን ጥቀሱ።<br>• እግዚአብሔር እንዲሄዱ ወደ ሚፈልግበት ቦታ እንዲሄዱ ሲያሳያቸው የነበረው ማነው?<br>• በጳውሎስ ሕልም ምን ሆነ?<br>• ጳውሎስና የስራ አጋሮቹ ወደ መቄዶንያ የተጓዙት እንዴት ነበር?<br>• ጳውሎስና የስራ አጋሮቹ ሴቶቹን ያገኟቸው የት ነበር?<br>• ምን እያደረጉ ነበር?<br>• የልዲያ ስራዋ ምን ነበር?<br>• ልዲያ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ስትሰማ ምን አደረገች? |

## <u>ሀ11 ታሪክ 4</u>

## ጳውሎስና ሲላስ በወህኒ ቤት – ይህ ታሪክ በኢየሱስ ስላመኑ ተጨማሪ ሰዎች የሚናገር ታሪክ ነው።

**በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**

- ለመዳን በኢየሱስ ክርስቶስ ማመን እንዳለብን እንማራለን።
- ክርስቲያኖች ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስላላቸው ደስተኞች እንደሆኑ እንማራለን።

**ቁልፍ ጥቅስ** **የሐዋርያት *ሥራ* 16: 31**

**የጥናት ክፍል :** **የሐዋርያት *ሥራ* 16: 16-34**

### *መግቢያ*

- *ተማሪዎቻችሁን ደስተኛ የሚያደርጋቸው ምን እንደሆነ ጠይቋቸው።*
- *በዛሬው ታሪክ ደስተኛ ሰዎች እንዳሉ ንገሯቸው። በጥንቃቄ አድምጠው ደስተኛው የተባሉት እነማን እንደነበሩ መናገር እንዳለባቸው ንገሯቸው።*

### የማስተማር ጊዜ

- *አንድ ቀን ጳውሎስና ሲላስ አንዲት በፊልጵስዩስ የምትኖር የቤት ሰራተኛ የሆነች ሴትን ረዷት። የዚህች የቤት ሰራተኛ አሳዳሪዎችን እጅግ አበሳጫቸው። ጳውሎስንና ሲላስን ጎትቶ ወደ ከተማይቱ የገበያ ስፍራ ወሰዳቸው። በዚያም ስለ እነርሱ በሐሰት ተናገረ።* **(የሐዋርያት *ሥራ* 16: 16-21)**
- *ጳውሎስና ሲላስ ተደበደቡ። ከዚያም በወህኒ ቤት ተጣሉ። የወህኒ ጠባቂውም እጆቻቸውን በሰንሰለት አሰራቸው። እግራቸውን ከከባድ ግንድ ጋር አጣበቀው።* **(የሐዋርያት *ሥራ* 16: 22-24)** *አሁን ጳውሎስና ሲላስ ምን የሚሰማቸው ይመስላችኋል?*
- *በእኩለ ሌሊት ሌሎች እስረኞች እየሰሟቸው ጳውሎስና ሲላስ እግዚአብሔርን እያመሰገኑ ይዘምሩ ነበር! ምንም እንኳን ጀርባቸው ከደረሰባቸው ድብደባ የተነሳ ቢቆስልም እግዚአብሔርን ማመስገናቸውን አላቋረጡም።* **(የሐዋርያት *ሥራ* 16: 25)**
- *በድንገት እንግዳ ድምፅ ተሰማ። ሁሉም ነገር ተናወጠ፣ ደግሞም እየወደቀ ተሰባበረ። የመሬት መንቀጥቀጥ ነበር። በሮች ተከፈቱ። ሰንሰለቶች ወደቁ።* **(የሐዋርያት *ሥራ* 16: 26)**
- *የወህኒ ጠባቂው ነቃ። ሁሉም የወህኒው ደጆች ተከፍተው አየ። ይህን ሲያይ በመጀመሪያ ሊያስብ የሚችለው ምንድነው ትላላችሁ? እስረኞቹ ሁሉ በዚያ ስለ ነበሩ ጳውሎስ ስጋት እንዳይገባው ነገረው።* **(የሐዋርያት *ሥራ* 16: 27-28)**
- *የወህኒ ጠባቂው ኃጢአተኛ እንደሆነ ስለ ተረዳ ጳውሎስን ለመዳን ምን ማድረግ እንደሚገባው ጠየቀው። ጳውሎስን "በጌታ በኢየሱስ እመን ትድናለህ" አለው። ጳውሎስና ሲላስ ለወህኒ ጠባቂው ኢየሱስ ክርስቶስ በእርሱና በቤተ ሰቡ ኃጢአት ምክንያት በመስቀል ላይ መሞቱን ገለፀለት። ወህኒ ጠባቂው ጳውሎስንና ሲላስን ወደ ቤቱ ወሰዳቸው። ቁስላቸውንም አጠበላቸው። ምግብም አቀረበላቸው። በኢየሱስ ክርስቶስ ስላመኑ ለወህኒ ጠባቂውና ለቤተ ሰቦቹ ያቺ ምሽት የደስታ ምሽት ሆነችላቸው።* **(የሐዋርያት *ሥራ* 16: 29-34)**
- *በዚህ ታሪክ ውስጥ ደስተኛው ማን ነበር? የደስታቸው ምክንያት ምን ነበር? (ተማረዎቻችሁ ስለ ጳውሎስና ስለ ሲለስ እንዲያወሩ አበረታቷቸው። የእነኝህ ሰዎች የደስታ ምክንያት በኢየሱስ መዳናቸው መሆኑን ንገሯቸው።)*
- *እኛም ከኃጢአታችን መዳን እንዳለብን ለተማሪዎቻችሁ ንገሯቸው። በኢየሱስ የምናምነው ስለ እኛ የሞተው የእግዚአብሔር ልጅ ስለሆነ ነው።*

**የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን አጠናቁ።**

### *የመማር ጊዜ*

ቁልፍ ጥቅሱን እንደአስፈላጊነቱ አስተምሩ፣ አብራሩ። - **የሐዋርያት *ሥራ* 16: 31**

### REMEMBER IT

- *ጳውሎስና ሲላስ የረዱት ማንን ነበር?*
- *ጳውሎስና ሲላስ ምን ደረሰባቸው?*
- *በእኩለ ሌሊት ጳውሎስና ሲላስ ምን እያደረጉ ነበር?*
- *ሲዘምሩ ምን ሆነ?*
- *የወህኒ ጠባቂው በመሬት መንቀጥቀጡ ምክንያት የደነገጠው ለምን ነበር?*
- *የወህኒ ጠባቂው ጳውሎስንና ሲላስን ምን ጠየቃቸው?*
- *ጳውሎስና ሲላስስ ምን ነገሩት?*
- *በዚያን ምሽት የወህኒ ጠባቂው ምን አደረገ?*
- *ከዚህ እኛ የምንማረው ምንድነው?*

<u>ሀ12 ታሪክ 1</u>

**ዘካርያስና ኤልሳቤጥ – ይህ ታሪክ እግዚአብሔር ፀሎትን እንደሚመልስ የሚናገር ታሪክ ነው።**

| | |
|---|---|
| | **በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>• እግዚአብሔር ፀሎትን እንደሚመልስ እንማራለን።<br>• ፀሎት የሚመለሰው እግዚአብሔር በመረጠው ጊዜ እንጂ እኛ በመረጥነው ጊዜ እንዳልሆነ እንማራለን።<br>**ቁልፍ ጥቅስ** **ሉቃስ 1፡ 13**<br>**የጥናት ክፍል :** **ሉቃስ 1፡ 5-25** |
| *መግቢያ* | • *ተማሪዎቻችሁን ስለ ቤተ ሰቦቻቸው እንዲነግሯችሁ ጠይቋቸው።*<br>• *በቤተ ሰቦቻቸው ወይንም ደግሞ በዘመዶቻቸው ውስጥ ስለ ሚገኙ ሕፃናት ከተማሪዎቻችሁ ጋር ተወያዩ። ሕፃናት ሰዎችን ያስደስታሉ።*<br>• *ተማሪዎቻችሁ በጣም ስለ ሚወዱት ነገር እንዲነግሯችሁ ጠይቋቸው። ለምን እንደሚወዱት ሊነግሯችሁ ይችላሉ?* በዚህ ታሪክ ውስጥ የተጠቀሱት ጥንዶች ይህ ስሜት ተንፀባርቆባቸው ነበር። ልጅ በጣም ይፈልጉ ነበር። |
| የማስተማር ጊዜ | • ዘካርያስና አልሳቤጥ ልጅ እንዲኖራቸው እጅግ በጣም ይፈልጉ ነበር። እያረጁ ሲሄዱ ወዳጆቻቸው በሙሉ ቤተ ሰብ አላቸው እነርሱ ግን ልጅ አልባ ነበሩ። *ምን የሚሰማቸው ይመስላችኋል? ልጅ ስለ ሌላቸው የቀረባቸው ነገር ምን ይሆን? ተማሪዎቻችሁ በባሕላቸው ላይ ተመስርተው የተለያዩ አስተያየቶችን እንዲሰጡ እድል ፍጠሩላቸው።* **(ሉቃስ 1፡ 5-7)**<br>• ስለዚህ ጉዳይ ወደ እግዚአብሔር ለመፀለይ ወሰኑ። እግዚአብሔር ፀሎትን እንደሚመልስ ያውቁ ነበር! **(ሉቃስ 1፡ 13)** *ስላለብን ማንኛውም ችግር መፀለይ እንደምንችል ጥቀሱላቸው።*<br>• እግዚአብሔር ፀሎታቸውን ሰምቶ ዘካርያስ በመቅደስ እያገለገለ ሳለ መልአኩን ላከው። *መልአኩ ሲገለጥ ዘካርያስ ምን የሚሰማው ይመስላችኋል?* መልአኩም ዘካርያስን አትፍራ አለው። ኤልሳቤጥ እንደምትፀንስና ወንድ ልጅ እንደምትወልድ ስሙንም ዮሐንስ እንደሚሉት ነገረው። **(ሉቃስ 1፡ 8-11)**<br>• ዘካርያስ የተነገረውን ዜና ማመን አልቻለም። እርሱና ሚስቱ ኤልሳቤት ስላረጁ ልጅ መውለድ እንደማይችሉ አሰበ። ከእግዚአብሔር ይዞት የመጣውን መልእክት ስላላመነ ልጁ እስከሚወለድ ድረስ ዱዳ እንደሚሆን መልአኩ ነገረው። **(ሉቃስ 1፡ 18-20)**<br>*ከዘካርያስ እጅግ በጣም አስፈላጊ ትምህርት እንማራለን። ... ስንፀልይ እግዚአብሔር ፀሎታችንን እንደሚመልስ ማመን አለብን። ዛሬ ሊፀለይባቸው የሚገቡ ጉዳዮችን አስቡ!*<br>**የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን አጠናቁ።** |
| *የመማር ጊዜ* | ቁልፍ ጥቅሱን እንደአስፈላጊነቱ አስተምሩ፣ አብራሩ። - **ሉቃስ 1፡ 13** |
| የክለሳ ጊዜ | • ዘካርያስ ማንን ነበር ያገባው?<br>• ባልና ሚስቶቹ የሚሹት ምን ነበር?<br>• ዘካርያስና ኤልሳቤጥ ወደ ማን የፀለዩት ነበር?<br>• ዘካርያስን በመቅደሱ ሊገናኘው የመጣው ማን ነበር?<br>• መልአኩ ሲገለጥለት ዘካርያስ ምን ተሰማው?<br>• የመልአኩ መልእክት ምን ነበር?<br>• ዘካርያስ የመጣውን መልእክት ስላላመነ ምን ደረሰበት?<br>• ስንፀልይ ልናደርገው የሚገባ በጣም አስፈላጊ ነገር ምንድነው? |

ሀ12 ታሪክ 2

ማርያምና ገብርኤል – ይህ ታሪክ ማርያም እግዚአብሔር የተናገራትን ነገር ስለ ማመኗ ይናገራል።

| | |
|---|---|
| | **በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>• ማርያም በመልአኩ በኩል የመጣው የእግዚአብሔር መልእክት የማይሆን ቢመስላት ተቀብላ ማመኗን እንማራለን።<br>• እግዚአብሔር ለሰው የማይቻሉ ነገሮችን ማድረግ እንደሚችል እንማራለን።<br>**ቁልፍ ጥቅስ** ሉቃስ 1፡ 37<br>**የጥናት ክፍል ፡** ሉቃስ 1፡ 26-38 |
| *መግቢያ* | ባለፈው ትምህርታችን ያየነውንና መልአኩ ለዘካርያስና ለኤልሳቤጥ ልጅ እንደሚወለድላቸው ያመጣውን መልእክት ታሪክ ከልሱላቸው። ይህ መልእክት ለዘካርያስና ለኤልሳቤጥ ከመጣላቸው ከጥቂት ቀናት በኋላ እግዚአብሔር ያንኑ መልአክ ወደ ሌላ ሰው ላከው። |
| *የማስተማር ጊዜ* | • *ማርያንም ከኤልሳቤጥ ጋር አወዳድሯት።* ማርያም ወጣት ነች። ከናዝሬት ከተማ ለሆነ ዮሴፍ ለሚባል ሰውም ታጭታለች። አንድ ቀን መልአኩ ገብርኤል ሊጎበኛት መጣ። (**ሉቃስ** 1፡ 26-27) *ይህ የተለመደ ነገር እንዳልሆነና ማርያምም ልትፈራ እንደምትችል ለተማሪዎቻችሁ አስረዷቸው።*<br>• መልአኩም መፍራት እንደማይገባት ነገራት። ገብርኤል ወንድ ልጅ እንደምትወልድ ሲያበስራት በጥሞና አደመጠችው። ማርያም በጥቂቱም ቢሆን መደናገጧ አልቀረም። ምክንያቱም ገና ትዳር አልያዘችም። ወይንም ባል የላትም። መንፈስ ቅዱስ ይህንን ልዩ ሕፃን እንደሚሰጣት ነገራት። ስሙንም ኢየሱስ ብላ መጥራት እንደሚገባት አስታወቃት። (**ሉቃስ** 1፡ 29-34)<br>• ኢየሱስ በምድር ላይ ከተወለዱት ህፃናት ሁሉ ይልቅ እንደሚበልጥ ነገራት። የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል። ለመረዳት አስቸጋሪ ቢሆንም ለእግዚአብሔር የሚሳነው ምንም ነገር እንደሌለ ነገራት። (**ሉቃስ** 1፡ 35-37)<br>• ማርያም ከመልአኩ የሰማቸውን መልእክት አምና ተቀበለችው። ማርያም እግዚአብሔር ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ወደዚህ አለም ለመላክ ባለው ትልቅ እቅድ ውስጥ ለመሳተፍ ፈቃደኛ ሆነች። የኢየሱስ ክርስቶስ ውልደት አስደናቂ ተአምር እንደሚሆን ይጠበቅ ነበር። (**ሉቃስ** 1፡ 38)<br>• *ለማመን የሚከብዳቹድሁ ነገር ቃል ተገብቶላችሁ ያውቃል?*<br>• *ማርያም መልአኩን ለምን አመነችው? ልክ እንደማርያም እኛም ሁላችንም እግዚአብሔርን ልናምነው ይገባናል።*<br>**የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን አጠናቁ።** |
| *የመማር ጊዜ* | ቁልፍ ጥቅሱን እንደአስፈላጊነቱ አስተምሩ፣ አብራሩ። - **ሉቃስ** 1፡ 37. ተማሪዎቻችሁ ሌሎች "አስቸጋሪ" የሚባሉና እግዚአብሔር ግን ያሳካቸውን ነገሮችን ማሰብ ይችላሉ? እግዚአብሔር ሁሉን የሚችል ብርቱ አምላክ ስለሆነ አመስግኑት! |
| *የክለሳ ጊዜ* | • ማርያም ትኖር የነበረው የት ነበር?<br>• ማርያም ያገባቸው ማንን ነበር?<br>• ማርያምን ሊጎበኝ የመጣው መልአክ ማን ይባል ነበር?<br>• መልአኩ ይዞላት በመጣው መልእክት ምክንያት ለምንድነው ማርያም ግራ የተጋባቸው?<br>• የሚወለደውን ሕፃን ልዩ የሚያደርገው ምንድነው?<br>• ማርያም ስለ መልእክቱ ምን አደረገች?<br>• ማርያም ለእኛ በምንድነው ጥሩ ምሳሌ የምትሆንልን?<br>• ለእግዚአብሔር የሚከብዱት ነገሮች ምንድናቸው? |

## *ሀ12 ታሪክ 3*

### የዮሐንስ ውልደት – ይህ ታሪክ የእግዚአብሔር የተስፋ ቃል ፍፃሜ እንደሚያገኝ የሚናገር ታሪክ ነው።

| | |
|---|---|
| | **በዚህ ክፍል የምንማራቸው የሚከተሉትን ነው።**<br>• *እግዚአብሔር ለዘካርያስና ለኤልሳቤጥ የገባውን ቃል ኪዳን እንደፈፀመ እንማራለን።*<br>• *ለእኛም የገባልንን ቃል እንደሚፈፅምልን እንማራለን።*<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ** **ሉቃስ** 1: 76<br>**የጥናት ክፍል :** **ሉቃስ** 1: 57-80 |
| *መግቢያ* | • *ለረዥም ወራት ሳይናገሩ ዱዳ ሆኖ መቆየት ምን እንደሚመስል ተወያዩበት። ይህ ታሪክ ዘካርያስ ባለማመኑ ስለ ደረሰበት ነገር እንደሚናገር ተማሪዎቻችሁን አስታውሷቸው።*<br>• *በክርስቶስ ልደት (በገና) ወይንም ደግሞ ልደታችሁ በሚከበርበት ማለዳ ስትጠብቁት የነበረውን ስጦታ ስታገኙ ምን ሊመስል እንደሚችል ተናገሩ? ዘካርያስና ኤልሳቤጥ ልክ መልአኩ እንደተናገረው ልጅ ሲወልዱ የተሰማቸው እንዲህ ነበር። በጣም ልዩ ቀን ነበር ለእነርሱ!* |
| *የማስተማር ጊዜ* | • *ሕፃኑ ሲወለድ ቤተ ሰቦቹና ጎረቤቶቹ እንደአባቱ ዘካርያስ ተብሎ እንዲጠራ ፈልገው ነበር። ኤልሳቤጥ ግን ስሙ መሆን ያለበት ዮሐንስ ነው አለች።* (**ሉቃስ** 1: 57- 60) *ለምንድነው ኤልሳቤጥ ዮሐንስ ተብሎ እንዲጠራ የፈለገችው?*<br>• *ዘካርያስም ልጁ ማን ተብሎ መጠራት እንዳለበት ሲጠየቅ በወረቀት ላይ "ስሙ ዮሐንስ ነው" ብሎ ፃፈ።* (**ሉቃስ** 1: 62-63)<br>• *ልክ በዚያች ሰዓት መናገር ቻለ። ዘካርያስ እግዚአብሔርን አመሰገነ፣ አከበረም። ዘካርያስ ይህን የሚያደርግበት ምክንያት ምንድነው? እግዚአብሔር የተስፋ ቃሉን ጠብቋል። ልጁ በመወለዱ በጣም ደስተኛ ነበር። እንዲሁም ሕፃኑ ሚደግ ሲጀምር እግዚአብሔር በሕፃኑ ድንቅና ተአምራትን ያደርጋል። ባዩት ነገር ሁሉም ሰዎች ተደነቁ።* (**ሉቃስ** 1: 64-66)<br>• *ዮሐንስ የተለየ ልጅ ነበር። ለምን? ወላጆቹ ይህን ሕፃን ለብዙ አመታት ሲጠብቁ እንደቆዩ ለተማሪዎቻችሁ ንገሯቸው። ወይንም ከዚህ ይልቅ እጅግ የሚበልጠውን ለሚመጣው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ መንገድን በመጥረግ ለማዘጋጀት እንደሚያድግ ንገሯቸው።*<br>• *እግዚአብሔር ለእኛም የገባውን ቃል እንደሚፈፅም ማወቅ አለብን። ለእኛ በመጽሐፍ ቅዱስ የገባልንን የተወሰኑ የተስፋ ቃላት ጥቀሱላቸው።*<br><br>**የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን አጠናቁ።** |
| *የመማር ጊዜ* | *ቁልፍ ጥቅሱን እንደአስፈላጊነቱ አስተምሩ፣ አብራሩ።* - **ሉቃስ** 1: 76. *ይህ ጥቅስ እግዚአብሔርን ለማመስገን ከተቀኘው ቅኔ የተወሰደ እንደሆነ ግለፁላቸው።* |
| *የክለሳ ጊዜ* | • *የኤልሳቤጥ ባል ስሙ ማን ነበር?*<br>• *መናገር ያልቻለበት ምክንያቱ ምን ነበር?*<br>• *ጎረቤቶቹ ሕፃኑ ማን ተብሎ እንዲጠራ ይፈልጉ ነበር?*<br>• *ዘካርያስና ኤልሳቤጥ ሕፃኑን ዮሐንስ ተብሎ እንዲጠራ የፈለጉት ለምን ነበር?*<br>• *ዘካርያስ እንደገና መናገር የጀመረው መቼ ነበር?*<br>• *የዮሐንስ ልዩ አገልግሎት ምን ነበር?*<br><br>**አዘጋጁ።** *ተማሪዎቻችሁ የዮሐንስን ውልደት አስመልክቶ የምስራች ካርድ ማዘጋጀት ይችላሉ።* |

## ሀ12 ታሪክ 4
## የኢየሱስ ክርስቶስ ውልደት – ይህ ታሪክ  እግዚአብሔር ልጁን ስለ መስጠቱ የሚናገር ታሪክ ነው።

| | |
|---|---|
| | **በዚህ ክፍል የምንማራቸው  የሚከተሉትን ነው።**<br>• የእኛ አዳኝ ለመሆን የመጣው ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ እንማራለን።<br>• እግዚአብሔር እኛን ከመወደዱ የተነሳ ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ስለ ላከልን ማመስገን እንደሚገባን እንማራለን።<br><br>**ቁልፍ ጥቅስ        ሉቃስ 2: 7**<br>**የጥናት ክፍል :     ሉቃስ 2: 1-7** |
| *መግቢያ* | • እቅዶች በመጨረሻዋ ደቂቃ ላይ እንዴት ሊለወጡ እንደሚችሉ ተነጋገሩ። አሁን ካላችሁበት አውድ ጋር አብሮ መሄድ የሚችል ምሳሌ ስጧቸው። ይህም በእናንተ ወይንም በተማሪዎቹ ተሞክሮ ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት።<br>• የማርያም ልጅ የሚወለድበት ጊዜ እየተቃረበ እንደሆነ ግለፁላቸው። ሕፃኑ ማርያምና ዮሴፍ በሚኖሩበት በናዝሬት ከተማ ውስጥ ቢወለድ ይቀል ነበር። |
| የማስተማር ጊዜ | • የሮማው ገዢ ሰዎች ሁሉ ወደ ተወለዱበት ከተማ ወይንም መንደር ሄደው እየተካሄደ በነበረው የሕዝብ ቆጠራ ላይ እንዲቆጠሩ ትዕዛዝ አወጣ። ዮሴፍና ማርያም በዚህ አዋጅ ምክኒያት ወደ ቤተ ልሔም መሄድ ነበረባቸው። (**ሉቃስ 2: 1-5**) *ምን ያህል ርቀት እንደተጓዙ ማየት እንዲችሉ እርዷቸው።  ምናልባትም ርቀቱ  በግምት 120 ኪ.ሜ ሊሆን ይችላል። ወይንም ደግሞ በእግር የአራት ቀናት ጉዞ ሊሆን ይችላል። ይህን ረዥም ጉዞ መጓዝ ምን ሊመስል ይችላል?*<br>• እንደረሱ ከተማይቱ በሰው ተጨናንቃለች። የሚያርፉበትን ቦታ ማግኘት አልቻሉም። በዚያ ላይ ደግሞ ሕፃኑ የሚወለድበት ጊዜ እየተቃረበ ነው።  በከብቶች  በረት ውስጥ ለማረፍ ተገደዱ።  (**ሉቃስ 2: 6-7**)<br>• ሕፃኑ ኢየሱስ ሲወለድ በጨርቅ ተጠቅልሎ በከብቶች ግርግም ላይ እንዲተኛ ተደረገ። ግርግም ማለት እንስሳቱ የሚመገቡበት ሰፋ ያለ እቃ ማለት ነው። (**ሉቃስ 2: 6-7**)<br>• *ኢየሱስ በጨርቅ የተጠቀለለውና በከብቶች መመገቢያ ላይ እንዲተኛ የተደረገው ለምንድነው? በዝቅተኛ ስፍራ የተወለደው ይህ ሕፃን ታላቅ ሕፃን እንደሆነ እንዲገነዘቡ እርዷቸው።  አንድ ሕፃን ሲወለድ በባሕላችሁ የሚደረግለትን ነገር አሁን ለኢየሱስ እየተደረገለት ካለው ነገር ጋር አነፃፅሩ።*<br>• *እንደኢየሱስ ያለሕፃን ከዚያ በፊትም ሆነ ከዚያ በኋላ አልተወለደም። እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ ነው። እኛን ለማዳን ከሰማየ ሰማያት ለመውረድና በምድር ላይ ተወልዶ እኛን ከኃጢአት ለማዳን ፈቃደኛ ነበር።* (**ማቴዎስ 1: 21**)<br>• *ገና (የክርስቶስ የልደት በዓል) ዋነኛ አላማው ይህ መሆኑን አዝዝጉ። ከታላቅ ፍቅሩ የተነሳ ልጁን ኢየሱስ ክርስቶስን ልኮ ስላዳነን እግዚአብሔርን ልናመሰግነው ይገባናል።*<br><br>**የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶችን አጠናቁ።** |
| የመማር ጊዜ | ቁልፍ ጥቅሱን እንደአስፈላጊነቱ አስተምሩ፣ አብራሩ።  - **ሉቃስ 2: 7** |
| የክለሳ ጊዜ | • ዮሴፍን ያገባቸው ማን ነበረች?<br>• ዮሴፍና ማርያም የሚኖሩት የት ነበር?<br>• ዮሴፍና ማርያም የተጓዙት የት ነበር?<br>• ዮሴፍና ማርያም  ምን ያደርጉ ነበር?<br>• በከብቶች በረት ለማረፍ የተገደዱት ለምን ነበር?<br>• ሕፃኑ ኢየሱስ የተኛው በምን ውስጥ ነበር?<br>• ኢየሱስን ልዩ የሚያደርገው ምንድነው?<br>• አዳኝ ለምን ያስፈልገናል? |

# ለመምህራን የእርማት መመሪያ

**ለደረጃ 1 ትምህርቶች**

- በሳምንት አንድ ገፅ (ወይንም በእያንዳንዱ ጥራዝ ሁለት ገፆች) ይሰጣቸዋል። ይህም በዋነኝነት ቀለም መቀባትና የጎደሉ ቃላት መሙላትን ይይዛል።
- በየሳምንቱ 10 ነጥብ ይሰጣል። ወይንም በወር ቢበዛ 40 ነጥብ ብቻ ያገዝላቸዋል።
- የደረጃ 1 ተማሪዎች ብዙ እንዲያነቡ ስለ ማይጠበቁ ወላጆች/ሕጋዊ አሳዳጊዎች/ እንዲሁም መሪዎች እርዳታ እንዲሰጧቸው ይጠበቃል።
- ለአንድ መልስ ሁለት ነጥብ ይሰጣል። እንዲሁም በእያንዳንዱ ትምህርት ለቀለም ቅብ 10 ነጥብ ይሰጣል።

**ደረጃ 2 ትምህርቶች:**

- በሳምንት 2 ገፆች ወይንም ደግሞ በአንድ ጥራዝ 4 ገፆች ይሰጣቸዋል።
- ታሪኮቹ የሚገኙት በየትምህርቶቹ ውስጥ ነው። ተማሪዎች የተለያዩ ቃላትን ከየትምህርቶቹ መፈለግ፣ የቀለም ቅብ ስራ መስራትና ቁልፍ ጥቅሶችን ማሟላት ወዘተ... ይጠበቅባቸዋል።
- ልክ ትምህርቶቹ ሲጠናቀቁ በየሳምንቱ ሀያ ነጥቦ በወር ደግሞ ቢበዛ 80 ነጥቦች ሊሰጡ ይገባል።

**የዘመነ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች ነጥብ አሞላል**

**የነጥብ አሞላል ፍንጮች**

መምህራን በመጀመሪያ የሚከተሉትን እንዲያደርጉ ይጠየቃሉ።

- እያንዳንዱን ትምህርት መገምገምና መልሶቹ ትክክል መሆን አለመኖናቸውን ምልክት ማድረግ።
- በመመሪያው መሰረት ትክክለኛውን ነጥብ መስጠት።
- ነጥብ ስንሰጥ የተለያየ አይነት ቀለም ያላቸውን ብዕሮች /እስክርቢቶዎች/ መጠቀም አለበን። ትክክል ለሆኑ መልሶች የ "✓" ምልክት እናድርግ።
- ትክክል ላልሆኑ መልሶች ትክክለኛ መልሶቻቸውን አስቀምጡ። የፊደላት ግድፈቶች ካሉም እርማት ስጡ። ለፊደላት ግድፈት ነጥብ አይቀነስም።
- በከፊል ትክክል ለሆኑ መልሶች ነጥብ ቀንሱ።
- የወሩን ድምር ነጥብ አስቀምጡ። ይህንንም በጀርባ ገፅ ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀው ክፍት ቦታ ላይ ፃፉ።

አንዳንዴ በአግባቡ ሊጋስ መሆን ያስፈልጋል። እንዲሁም ተማሪዎች የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቱን ማጠናቀቅ እንዲችሉ ለማበረታታት ማንኛውንም ነገር ማድረግ አስፈላጊ ነው። በየወሩ መጨረሻ መምህራን አንድ የማበረታቻ ቃል ለተማሪዎች ቢፅፉ መልካም ነው። ይህን ለማድረግም በየትምህርቶቹ ቦታ ተዘጋጅቷል። ጥሩ የቀለም ቅብን፣ ንፅሕናን፣ ተማሪው ያስመዘገበውን ነጥብ፣ ተማሪው ምን ያህል እንደተረዳ የሚገልፁ አስተያየቶችን መፃፍ ይቻላል።

አስተያየቶች በተቻለ መጠን የተለያዩ እንዲሆኑ መጣር አለብን። ጥያቄዎች፣ አረፍተ ነገሮች፣ ምልከታዎች፣ ማበረታቻዎች ወዘተ...ይህን ልዩነት ለማሳየት ልንጠቀምባቸው እንችላለን። ይህ በጥልቅ ማሰብንና የተማሪዎች ፍላጎት መጠበቁን ማረጋገጥ ይጠይቃል። አንድ አረፍተ ነገር ወይንም ደግሞ ጥያቄ በየወሩ የሚደጋገም ከሆነ የሚፈለገውን ግብ ላይመታ ይችላል።

**ደረጃ 1**

**አጠቃላይ አስተያየቶች**

"ኤሚ ይህን ትምህርት በመጀረሽ በጣም ደስተኛ ነኝ። እንዲሁም በትምህርቶቹ በጣም ደሰተኛ እንደሆንሽ እርግጠኛ ነኝ። የቀለም ቅብሽ አስደስቶኛል። ትምህርት ቤት እየሄድሽ ነው ወይ? እስኪ ስለ ትምህርት ቤትሽ ንገሪኝ። መልስሽን በናፍቆት እጠብቃለሁ።"

"እንድርያስ! እጅግ በጣም ግሩም ስራ ነው። የሚገርም ቅብ ነው! መስመር መጠበቅ ከባድ ነበር እንዴ? አንድ ቅብ ሊያርፍበት የሚገባውን ቦታ የዘነጋኸው አይመስልህም?"

**መንፈሳዊ አስተያየቶች**

"ሳራ! ግሩም ስራ! ኢያኢሮስ ኢየሱስ የረዳው ደስተኛ ሰው ነበር!"

"እጅግ በጣም ጥሩ መልሶች! የኢየሱስ ሞት ታሪኩ አሳዛኝ ቢሆንም ከሙታን መነሳቱ ደግሞ እጅግ አስደሳቹ ጫፍ ነው።"

**ደረጃ 2**

**አጠቃላይ አስተያየቶች**

" ዮናስ፣ መልስህ ጥሩ ነው። እርግጠኛ ነኝ የት/ቤት አስተማሪዎችህ በአንተ እጅግ በጣም ደስተኞች እንደሆኑ እርግጠኛ ነኝ።"

"ብሩክ! የልደት ቀንህ እየደረሰ እንደሆነ አውቄአለሁ። ለልደትህ ልዩ ዝግጅት እያደረግህ ነው? ምንም ነገር ብታደርግ መልካም ልደት እመኝልሃለሁ።"

"ጥረትህ በጣም አስገራሚ ጥረት ነው። ትንንሽዬ ስህተቶች አሉ። ሁልጊዜም መልሶችህን እንደገና አረጋግጥ።

**መንፈሳዊ አስተያየቶች**

"በበረት ውስጥ ያለውን ሕፃኑን ኢየሱስን የቀባሸበት መንገድ አስደስቶኛል። እግዚአብሔር ልጁን ወደ ዓለም ስለ እኛ መላኩ መልካም አይደለምን?

"ቅቦችህን በጣም ወድጃቸዋለሁ! እግዚአብሔር ያለውን ነገር ባለማመኑ ዘካሪያስን ዋጋ አስከፈለው። ከዚያ በኋላ የእግዚአብሔርን ቃል አልተጠራጠረም።"

"እጅግ በጣም አስደናቂ መልሶች! በምድረ በዳ ፊልጶስን የተገናኘው ሰው ደስተኛ ሆኖ ሄደ። ስለ ኢየሱስ መልካሙን ዜና ሰምቶ አመነ።

© የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርቶች አገልግሎት 2007ዓ.ም.

www.besweb.com

በሕግ የተመዘገበ የዩ.ኬ ሊጋሽ ድርጅት 1096157